# አዲስ ዘመን

እሁድ 84 ዓመት ቁጥር 047 ጥቅምት 17 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# “ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ያስቆጠረውን የኢትዮጵያና የማሌዢያ ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር ይገባል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**በአማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ያስቆጠረውን የኢትዮጵያና የማሌዢያ ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። የማሌዢያ የንግድ ማኅበረሰብ አባላት በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ዕድል እንዲሳተፉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ጥሪ አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከማሌዢያ አቻቸው አንዋር ኢብራሂም ጋር የሁለትዮሽ ውይይት ካደረጉ በኋላ ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ፤ ከጠቅላይ ሚኒስትር አንዋር ኢብራሂም ጋር የኢትዮጵያንና የማሌዢያን ሁለንተናዊ ግንኙነት ማሳደግ የሚያስችል ፍሬያማ ውይይት አድርገናል ብለዋል።

በኢትዮጵያ እና በማሌዢያ መካከል ያለው ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ የፈጀው የረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በተመሳሳይ የመሪዎች ጉብኝት ማጠናከር እንደሚገባም አመላክተዋል።

የግል ዘርፉ፣ የቱሪዝምና የመንግሥት ለመንግሥት ትብብሮች የሁለትዮሽ ግንኙነቱን ለማጠናከር ወሳኝ ድርሻ እንዳላቸው አስታውቀዋል።

የማሌዢያ የንግድ ማኅበረሰብ በፍጥነት በመስፋፋት ላይ ባለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን የኢንቨስትመንት ዕድል እንዲጠቀሙ አበረታታለሁ በማለትም ጥሪ አስተላልፈዋል።

ከማሌዢያ ወደኢትዮጵያ ለሚመጡ ባለሃብቶች መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማቅረብና ለመደገፍ ቁርጠኛ ነው መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ከማሌዢያ ስለፌዴራል መንግሥት ሥርዓት፣ ከተሞችን በማዘመን እና በመሠረተ ልማት ግንባታ ዙሪያ ብዙ የምትማራቸው ጉዳዮች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

በማሌዢያ የሁለት ቀናት ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

“ከግማሽ ምዕተ ዓመት ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል












አብርሃም በላይ (ዶ/ር)

## የ46 ሚሊዮን ዶላር ፕሮጀክቶቹ የመስኖ ልማትን ለማሳደግ ዓይነተኛ ሚና አላቸው

ገጽ 5

# የባሕር በርና ዓለም አቀፍ ሕግጋት

**ዘላለም ግዛው**



ቀደም ባሉ ዘመናት አንዳንድ የሕግ ሊቃውንቶች በተለይም ውቅያኖሶችና መሰል የውሃ አካላትን በማንም ሀገር ቁጥጥር ስር ሊሆኑ እንደማይችሉና ለማንም ሊሆኑ እንደሚገባ መከራከሪያ አቅርበው ነበር። በዚህ የዓለም አቀፍ ሕግ መርሕ መሠረት የባሕር አካላትን በነፃነት መጠቀም የሚለውን መርሕ ፈጥረዋል።

እ.አ.አ. በ1982 የወጣው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፍ የባሕር ሕግ ደግሞ ሀገራት የባሕር ክልልና ወሰንን በምን መንገድ መጠቀም እንደሚገባቸው መሠረታዊ መርሆዎችን አስቀምጧል። ሕጉ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሀገራት መካከል የሚገኙ የውሃ አካላትን

የባሕር በርና ዓለም... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## የኮሪደር ልማቱ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማበልፀግ የመዳናዋን ዕድገት እያፋጠነ ይገኛል

ገጽ 5




ዜና

# የሀገር ውስጥ ማምረቻዎች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ ድጋፍ እየተደረገ ነው

## - ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት የገሊላ የጫማ ፋብሪካ ተመርቆ ሥራ ጀመረ

**ሞገስ ፀጋዬ**



አዲስ አበባ:- ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ሰፊ አበርክቶ ያላቸው የሀገር ውስጥ ማምረቻዎች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡

ገሊላ የጫማ ፋብሪካ ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ያስገነባውን ማምረቻ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ትናንትና አስመርቆ ሥራ አስጀመረ።

በወቅቱ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የኮርፖሬት ሀብት ማኔጅመንት ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ዓለማየሁ ሰይፉ እንደተናገሩት፤ የሀገር ውስጥ ማምረቻዎች ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ የሚረዱ የሕግ፣ የአሠራርና የመሥሪያ ቦታ ድጋፍ እየቀረበ ይገኛል።

እንደ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚው ገለጻ፤ ሀገር በቀል ድርጅቶች ምርቶቻቸውን ወደ ውጪ ልከው የሚያመጡት የውጪ ምንዛሪ የኢኮኖሚ ማሻሻያውን እንቅስቃሴ ያቀላጥፈዋል፡፡

ፋብሪካው በአጭር ጊዜ ጥራቱን ጠብቆ ተገንብቶ ወደ ሥራ መግባቱ ማምረቻዎች ለኢኮኖሚው ያላቸው አበርክቶ ለማሳደግ ያግዛል።

ወደ ሥራ የገባው የገሊላ የጫማ ፋብሪካ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት የኢኮኖሚ ማሻሻያውን በመደገፍ ረገድ የራሱ ሚና ይኖረዋል ብለዋል፡፡

ሌሎች ሀገር በቀል ድርጅቶችም ወደ ምርት በመግባትና ምርቶቻቸውን በማሳደግ የተጀመረው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ከዳር እንዲደርስ አስተዋፅዖ ማድረግ እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

በጫማ ማምረት ላይ የተሠማራው የገሊላ ጫማ ፋብሪካ የቆዳ ምርት የተሻለ ዋጋ እንዲኖረው ያደርጋል ያሉት አቶ ዓለማየሁ፤ በቆዳ ኢንዱስትሪ ውስጥ በመሳተፉ የቆዳ እሴት ሰንሰለት ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣል ሲሉ ጠቁመዋል።

ድርጅቱ በአጭር ጊዜ ወደ ምርት እንዲገባ ከኮርፖሬሽኑ ድጋፍ ነበር፤ ወደፊትም ይቀጥላል፡፡ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪዎች እንዲገቡ አርዓያ ይሆናል ብለዋል፡፡

በርካታ ኢንቨስትመንቶች ወደ ሀገር እንደሚገቡ የገለጹት አቶ ዓለማየሁ፤ ነገር ግን በተለያየ ጊዜና ምክንያት ኢንቨስትመንቶች ተመልሰው ከሀገር ይሸሻሉ፡፡ የገሊላ የጫማ ፋብሪካ ሀገር በቀል ድርጅት በመሆኑ ብዙ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ሲሉ አስረድተዋል።፡

በኢንዱስትሪያል ፓርኮች ውስጥ ለሚያለሙ የሀገር በቀል ድርጅቶች ጠንካራ ድጋፍ እንደሚደረግ በመግለጽ ባለሀብቶች እንዲያለሙ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የገሊላ ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ባለቤትና ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አሰፋ በርሄ እንደገለጹት፤ ተመርቆ ወደ ሥራ የገባው ማምረቻ በሰባት ሺህ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ሲሆን ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የተገነባ ነው፡፡

በቀን ሁለት ሺህ ጥንድ ጫማዎች የማምረት አቅም ያለው ድርጅቱ፤ ለአንድ ሺህ ሠራተኞች የሥራ ዕድል ፈጥሯል ብለዋል፡፡ ከሁለት ወር በኋላ የሠራተኞች ቁጥር ወደ አምስት ሺህ በማሳደግ በቀን አራት ሺህ ጥንድ ጫማዎችን ለሀገር ውስጥና ለተለያዩ የዓለም ሀገራት እንደሚያቀርብ አስታውቀዋል።

ኩባንያው የተለያዩ የሕጻናትና የአዋቂ ጫማዎችን ያመርታል ያሉት አቶ አሰፋ፤ በአውሮፓ፣ በአፍሪካ፣ ኤዥያና በሌሎች ሀገራትም የገበያ መዳረሻዎች መለየታቸውን ገልጸዋል፡፡

ድርጅቱ በመቀሌ የአውቶቡስ መገጣጠሚያ ፋብሪካ ከፍቶ ለመሥራት የመሠረት ድንጋይ ማስቀመጡን አመላክተው፤ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ማምረቻው የበኩሉን ጥረት እያሳደገ እንደሚሄድ አሳውቀዋል።



# በአዲስ አበባ የመንግሥትና የግሉን ዘርፍ የጋራ ኢንቨስትመንት ለማሳደግ ጥሪ ቀረበ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ:- በመዲናዋ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚከናወኑ የጋራ ኢንቨስትመንቶች ተሳትፎ ማሳደግ ያስፈልጋል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ ጃንጥራር ዓባይ ጥሪ አቀረቡ። ኖህ ሪል እስቴት 750 የመኖሪያ ቤቶችንና ሱቆችን አስመርቆ ለነዋሪዎች አስረከበ።

በወቅቱ የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ ጃንጥራር ዓባይ፤ ሀብትን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣትና የልማት ማነቆዎችን ለመቅረፍ በማለም አዲስ አበባ ለጋራ ኢንቨስትመንቶች ክፍት መሆኗን ገልጸዋል።

ከለውጡ በኋላ በቅርቡ የተካሄደውን የማክሮ ኢኮኖሚ ለውጥ ጨምሮ የተተገበሩ የሕግ ማዕቀፎች የመንግሥትና የግል ኢንቨስትመንቶችን በማጎልበት ሁለንተናዊ ልማትን ለማረጋገጥ የሚረዱ ናቸው ብለዋል።

ሦስተኛዋ ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲና ማዕከልና የአፍሪካ ኅብረት መገኛ በመሆኗ የነዋሪዎቿን ፍላጎት የሚያረካ ፈጣን ልማት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ጃንጥራር፤ የመልካም አስተዳደር፣ የሥራ ዕድል ፈጠራና የመሠረተ ልማት ጥያቄዎችን ለማሟላት የመንግሥትና የግል ዘርፍ የጋራ ጥረት አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል።

መንግሥት የመኖሪያ ቤቶችን ተደራሽነት ለማሳደግ ጥረት ቢያደርግም ከፍተኛ ፍላጎት በመኖሩ የሚፈለገውን ያህል ውጤት አለመምጣቱን አስታውሰው፤ ከመንግሥት ፕሮጀክቶች ጎን ለጎን በግል ኩባንያዎች እና በመንግሥትና የግል ባለሀብቶች የሚገነቡ የቤት ፕሮጀክቶችን ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ብለዋል።

የኖህ ሪል እስቴት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ፍቃዱ አዋሽ በበኩላቸው እንዳሉት፤ ኩባንያው መኖሪያ ቤቶችን በጊዜ እና በጥራት ገንብቶ በማጠናቀቅ ልምድ ማካበቱን ጠቁመዋል።

በቅርቡ በአዲስ አበባ እንቁላል ፋብሪካ በተሰኘ አካባቢ 750 መኖሪያ ቤቶች እንዲሁም በአቧሬ ሴቶች አደባባይ 152 ቤቶች ለነዋሪዎች እንደሚያስረክብ አመላክተዋል።

ሕንፃዎች በፍጥነት መገንባት ብቻ ሳይሆን ዘመናዊ የግንባታ ቡድን በማዘጋጀት፣ ዘመናዊ የኮንክሪት መሙያን በመጠቀምና የድርጅቱን የጥራት ላብራቶሪ በማቋቋም ለግንባታው ጥራት ከፍተኛ ቦታ መስጠቱን ተናግረዋል።

ሪል ስቴቱ ባለፉት 10 ዓመታት በ33 ሳይቶች 10 ሺህ የሚጠጉ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የመኖሪያ ቤቶችን ለቤት ፈላጊዎች ገንብቶ አስረክቧል ብለዋል።

በቀጣይ ወር በቦሌ ክፍለ ከተማ ቦሌ ሆምስ በተባለ አካባቢ ከአምስት ሺ በላይ የሚሆኑ ቤቶችን ግንባታ እንደሚያስጀምር ገልጸዋል።

# የእንስሳትን ጤና ለመጠበቅ ተጨማሪ ጥረት ያስፈልጋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ:- የእንስሳትን ጤናና ደኅንነት ለመጠበቅ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የዓለም የእንስሳት ቀን በኢትዮጵያ ለ14ኛ በዓለም ለ99ኛ ጊዜ "ለሰው ልጅ ደኅንነት እና ኢኮኖሚያዊ ብልፅግና በእንስሳት ደኅንነት ላይ ኢንቨስት እናድርግ" በሚል ሃሳብ በዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ተቋም ትናንት ተከብሯል።

በመድረኩ መልዕክት ያስተላለፉት በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ጤና እና ቬተርነሪ ፐብሊክ ሄልዝ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ውብሸት ዘውዴ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ የእንስሳትን ጤናና ደህንነት ለማረጋገጥ ሁሉም ባለድርሻዎች በትብብር መሥራት አለባቸው።



ውብሸት ዘውዴ (ዶ/ር)

የዓለም እንስሳት ቀን ሲከበር ትኩረት የሚያደርገው የእንስሳትን ደኅንነት ማስጠበቅ ላይ ነው ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ከአፍሪካ ቀዳሚ ብትሆንም የዘርፉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ጤናና ደኅንነታቸው ላይ አሁንም ብዙ መሥራት ይጠይቃል ብለዋል።

ደኅንነቱና ጤናው ያልተጠበቀ እንስሳን ለምግብነት መጠቀምም ሆነ ምርታማነቱ እንዲያድግ መጠበቀ አዳጋች መሆኑን ጠቅሰው፤ መንግሥት የእንስሳትን ጤና፣ ደኅንነትና በሽታ ቁጥጥር እንዲሁም የማኅበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሌማት ትሩፋት ፕሮግራም በተሠራው ሥራ በእንስሳት ምርትና ምርታማነት ላይ ትልቅ ውጤት መመዝገቡን አንስተው፤ ሥራው ውጤታማ እንዲሆን የእንስሳት ጤናና ደኅንነት መጠበቅ ይገባል ሲሉ አብራርተዋል።

የምርምር ተቋማት፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ሌሎችም ባለድርሻዎች በትብብር በመሥራት የእንስሳትን ጤና ለመጠበቅ መትጋት እንዳለባቸው አስረድተዋል።

ሥራዎችን በሕግ ማዕቀፍ ለመደገፍም የእንስሳት ጤናና ደኅንነት ረቂቅ አዋጅ መዘጋጀቱን ጠቁመው፤ ረቂቁ ሲፀድቅ ሙሉ በሙሉ ወደሥራ እንደሚገባ አመላክተል።

የኢትዮጵያ የእንስሳት ጤና ሐኪሞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ቦጃ እንደቦ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ የበርካታ ኢትዮጵያውያን ሕይወት ከእንስሳት ጋር የተገናኘ ነው። በመሆኑም እንስሳት ጤናና ደህንነት ላይ መሥራት ከሰዎች ሕይወት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው፡፡

የእንስሳት በሽታዎች ወደ ሰው እንደሚተላለፉ ጠቅሰው፤ የእንስሳትን ደኅንነት መጠበቅ የሰዎችን ጤና የማረጋገጥ አንድ አካል መሆኑን መገንዘብ ይገባል ብለዋል።

የእንስሳት ጤናና ደኅንነት የሚመራበት የሕግ ማዕቀፍ አለመኖር ዘርፉ ላይ ትልቅ ክፍተት ፈጥሮ መቆየቱን አስታውሰው፤ የእንስሳት ጤናና ደኅንነት ረቂቅ አዋጅ ፀድቆ ወደ ሥራ ሲገባ ችግሩን ይቀርፈዋል ተብሎ ይጠበቃል ሲሉ አመላክተዋል።

ከአጋር አካላት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን በአግባቡ ለመምራትና የባለሙያዎችን ደኅንነት ለማስጠበቅም አጋዥ ይሆናል ሲሉ ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሀገራቱ የጋራ ዕጣ ፈንታቸውን በጋራ የሚወስኑበት አዲስ የፖለቲካ ባሕል ያስፈልጋቸዋል

በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሠላም ለማምጣት፤ የአካባቢውን ሀገራት ሕዝቦች እውነተኛ ፍላጎት በአግባቡ መረዳት እና ለፍላጎታቸው በቅንነት እና በታማኝነት መሥራትን ይጠይቃል። ከዚህ ውጪ በአካባቢው ዘላቂ ሠላም ማስፈን እና ማፅናት ይቻላል ብሎ ማሰብ በራሱ ችግሮችን የሚያባብስ የተሳሳተ አካሄድ ነው።

አካባቢው ካለው ጂኦ ፖለቲካል ጠቀሜታ አኳያ፤ የብዙዎች ቀልብ የሚስብ፤ አይን ማረፊያ እና የትኩረት ምንጭ ነው። ከዚህ የተነሳ በየዘመኑ የተነሱ ኃያላን መንግሥታት ለአካባቢው ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ሲንቀሳቀሱ ተስተውለዋል። አሁንም አብዛኞቹ የዘመናችን ኃያላን መንግሥታት በአካባቢው ብሔራዊ ጥቅማችንን ለማስጠበቅ ያዋጣል የሚሉትን ሁሉ እያደረጉ ነው።

አካባቢው የዓለም የንግድ እንቅስቃሴ የደም ስር ከመሆኑ አኳያም፤ በአካባቢው ሊፈጠር የሚችል የበላይነት በአንድም ይሁን በሌላ፤ በዓለም አቀፍ ንግድ ውስጥ ያለውን የሀገራት ብሔራዊ ጥቅም የማስጠበቅ አቅም የሚያጎናጽፍ ነው። ይህ ደግሞ ባለንበት ዓለም የቱን ያህል ከፍያለ አጀንዳ ሊሆን እንደሚችል ለመገመት የሚከብድ አይደለም።

የአካባቢው ሀገራት በዚህ ዓለም አቀፋዊ እውነታ ውስጥ የራሳቸው ብሔራዊ ጥቅም የጉዳዩ አካል ያደርጋቸዋል። ከዛም ባለፈ አካባቢውን ለመቆጣጠር የሚደረጉ ትንቅንቆችን በስክነት ማየት ካልቻሉ የሌሎች አጀንዳ ተሻሚ በመሆን አላስፈላጊ ዋጋ መክፈላቸው የማይቀር ነው። ለዚህ ደግሞ ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት በአካባቢው የሚስተዋለውን ግጭት እና አለመረጋጋት ማየት በቂ ነው።

በየወቅቱ ወደ ሥልጣን የሚመጡ የአካባቢው ሀገራት መንግሥታት፤ የሕዝቦቻቸውን እውነተኛ ፍላጎት ወደኋላ በመተው፤ በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት የሌሎች አካላት/ኃይላት አጀንዳ መፈጸሚያ ሲሆኑ ማየት የተለመደ ነው። አሁን አሁን ችግሩ በአካባቢው የፖለቲካ ባሕል እየሆነ መጥቷል።

በርግጥ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች እውነተኛ ፍላጎት ካሉበት አንገት አስደፊ ድህነት እና ኋላቀርነት መውጣት ነው። ለዚህ የሚሆንም በቂ የተፈጥሮ እና የሰው ሀብት ባለቤቶች ናቸው። የሚፈልጉት እነዚህን ሀብቶች አቀናጅቶ ወደ ልማት የሚቀይር ፤ በተለወጠ ማንነት የተለወጠ ሀገር መፍጠር የሚችል የፖለቲካ አመራር ነው።

የሀገራቱ ሕዝቦች እውነተኛ መሻት፤ በሀገራቱ መካከል ለዘመናት የቆየውን ድንበር ተሻጋሪ ተፈጥሯዊ ወንድማማችነት፤ ተጨባጭ የልማት አቅም በማድረግ፤ የጋራ ዕጣ ፈንታቸውን በጋራ የሚወስኑበትን አዲስ የፖለቲካ ባሕል የሚፈጥር የፖለቲካ አመራር ነው።

የሀገራቱ ሕዝቦች ለዓመታት ካሳለፏቸው ግጭቶች እና ጦርነቶች፤ የሠላም ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ በተጨባጭ አይተዋል። ተስፋ ያደረጓቸው ትውልዶቻቸው ተስፋ ቢስ ሆነው ሲያልፉ አስተውለዋል፤ ብዙ ዋጋ ያስከፈሏቸው የፖለቲካ ትርክቶች ትርጉም የለሽ ሆነው አንገት አስደፍተዋቸዋል።

ግጭቶች እና ጦርነቶች ቀድሞ ከነበሩበት ድህነት እና ኋላቀርነት ወደከፋ ድህነት እና ኋላቀርነት ወስደዋቸዋል፤ ተመፅዋችነት ብሔራዊ መገለጫቸው፤ ጠባቂነት ዕጣ ፈንታቸው ሆኗል። አንዳንዶች የአክራሪ እና ፅንፈኛ ኃይሎች መፈልፈያ ሆነዋል። በዚህም በዛሬዎቻቸው ላይ የመወሰን አቅም አጥተው ተቸግረዋል።

የሕዝባቸውን የእለት ተእለት ሕይወት በሠላም የሚመሩበት ሀገራዊ አቅም አጥተው፤ እንደሀገር የከፋ ችግር ውስጥ ያሉ ፤ በሌሎች የሕይወት መስዋዕትነት ዛሬን እየኖሩ ያሉም አሉ። ይህ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች አሁናዊ ተጨባጭ እውነታ ነው ፤ የሕዝቦቹም እውነተኛ ፍላጎት ከዚህ ለዘለቄታው መውጣት ነው።

ለዚህ ደግሞ በአካባቢው ዘላቂ ሠላም ለማስፈን የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ያሉበትን ተጨባጭ እውነታ መረዳት ያስፈልጋል። ከዚህ ውጪ በእልህ እና በግትርነት፤ በሕዝቦች መካከል ጠላትነት እና ተቃርኖን በመስበክ፤ የሌሎችን አጀንዳ ስቦ በመሸከም በአካባቢው ዘላቂ ሠላም ማምጣት አይቻልም። በአካባቢው ዘላቂ ሠላም ማስፈን ካልተቻለ ደግሞ የሕዝቦቹን የመልማት ፍላጎት ተጨባጭ ማድረግ አይቻልም።

በመሆኑም የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦችን ካሉበት አንገት አስደፊ ድህነት እና ኋላቀርነት ለማውጣት ሠላምን እና የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ የፖለቲካ አስተሳሰብ እና የፖለቲካ አመራር ያስፈልጋል። በዚህም ሕዝቦቹ መካከል ለዘመናት የቆየውን ድንበር ተሻጋሪ ተፈጥሯዊ ወንድማማችነት፤ ተጨባጭ የልማት አቅም በማድረግ፤ የጋራ ዕጣ ፈንታቸውን በጋራ የሚወስኑበትን አዲስ የፖለቲካ ባሕል መፍጠር ይገባል። ያለው ብቸኛ አማራጭም ይሄው ነው።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የብሪክስ አባልነት-ከፍ ያለ የዲፕሎማሲ ድል

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

በአውሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር 2009 ላይ የጋርዮሽ የፖለቲካ ስብሰባ ያገናኛቸው አራት የተለያዩ ሀገራት በሩሲያ ምድር ላይ ታደሙ። ቻይና፣ ብራዚል፣ ሕንድና አዘጋጇ ሩሲያ ጭምር። ሀገራቱ በ2001 ላይ ተወጥኖ የቆየውን የብሪክስ ድርና እርሾ ዳግም አንስቶ ለመወያየት አልዘገዩም። በርካታ አጀንዳዎችን በመምዘዝ በጠንካራ ውይይትና ክርክር የተለያዩ ውሳኔዎችን በማሳለፍ አፀደቁ።

እነዚህ የቡድን ሀገራት ለጋራ ኅብረታቸው ሥያሜ ይሆን ዘንድ አንድ ገዢና ተፅዕኖ ፈጣሪ ስም መምረጥ ነበረባቸው። በጊዜው ለስያሜው የሚበጁ የተለያዩ ስሞች እንደ አማራጭ በዕጩነት ቀርበው ነበር። ቆይቶ ግን ሁሉንም በአንድ ሀሳብ የሚይዘው ስያሜ ልቦናቸውን ገዛ። ሀገራቱ በአንድ ሀሳብና ፍላጎት ስሙን ሊያጸኑት ተስማሙ። ለጋራ መጠሪያቸው ከየሀገራቸው ስም የመጀመሪያው ፊደል እንዲወሰድ ፈቅደው ቃሉን በይሁንታ አፀደቁ።

‹‹ብሪክስ ይሉት የስያሜ ምንጭ ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ሕንድና ቻይና ከተባሉት ሀገራት ላይ የተቀዳ ነው። ሁሉም ከመጀመሪያዎቹ ፊደላት አንደኛውን ለስያሜያቸው መጠሪያነት አዋጥተዋል። 2001 ላይ ተመሥርቶ የቆየው የብሪክስ ቡድን ሀገራት ከአንድ ዓመት በኋላ በ2010 ዳግም ሲገናኝ ደቡብ አፍሪካን በማከልና ቁጥሩን ወደ አምስት ከፍ በማድረግ ነበር።

የብሪክስ ቡድን ሀገራትን ለመመሥረት ምክንያት የሆኑ በርካታ ኢኮኖሚያዊ ነጥቦች ይነሳሉ። በዋንኛነት ግን የዓለም ፋይናንስ ሥርዓት በምዕራባውያን ሀገራት ከንድ ስር የመውደቁ እውነታ አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የአሜሪካ ዶላር የዓለማችን ብቸኛ መገበያያ ገንዘብ ሆኖ መዝለቁ ለቡድኑ መመሥረት አንዱ ምክንያት ነው።

የቡድን ሀገራቱ ለዘመናት ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ያመዘነው የዓለም ሥርዓት ሊበቃው ይገባል ሲሉ የመሠረቱት ኅብረት ውጤታማ እንደሚሆን አምነዋል። ይህ የብሪክስ ሀገራት እርምጃ ነባሩን የዓለም እንቅስቃሴ ማስደንገጡ አልቀረም። ብሪክስ ዓለም ዓቀፍ ተደማጭነትንና ትኩረትን በማግኘቱ የአባል ሀገራት ጠያቂዎችም ቁጥር እየጨመረ ሄደ።

በየጊዜው የሚስተዋለው የምዕራባውያን መልከ ብዙ ተፅዕኖ እንዳለ ሆኖ ለታዳጊ ሀገራት ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ጭምር ድምፅ ሆኖ ለመወከል የቡድኑ መመሥረት ወሳኝ የሚባል ሆኗል። በነዚህ ቡድን አባላት እሳቤ እንደ አይ.ኤም.ኤፍ እና የዓለም ባንክ የመሳሰሉ የፋይናንስ ተቋማት ለአሜሪካ ጥቅም ማስከበሪያ ሆነው ቆይተዋል። የተለያዩ ሀገራትን ኢኮኖሚ ለማዳከም ደግሞ በፖለቲካ የመጠቀም ስልታቸው የሚያህላቸው የለም።

አምስቱ የብሪክስ ሀገራት ለዘመናት ዓለምን በተፅዕኖ ተቆጣጥሮ የቆየውን የአሜሪካ ዶላር ግብይት በሌላ ገንዘብ የመተካት ዓላማን ይዘው ተነስተዋል። ከተቋቋሙበት ዕቅድ ውጭ የአሜሪካ ፖለቲካ መጠቀሚያ የሚሆኑ የፋይናንስ ተቋማትን ፈተና የሚያሸንፉ አቻዎችን የመመሥረት ትልም ይዘዋል።

የብሪክስ ቡድን ሀገራት 40 በመቶውን የዓለም ሕዝብ እንደሚይዙ ይነገራል። የአምስቱ ሀገራት የጋራ ምጣኔ ሀብትም የዓለምን 26 በመቶ ይሸፍናል። ይህ ሀብት በየግዜው የመጨመር አቅም አለው። በዓለም የንግድ እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖም ከፍተኛ ነው።

እነዚህ አምስት ሀገራት በዓለማችን ያላቸው የሀብት መጠንና የሕዝብ ብዛት ኃያል የሚባል ነው። ፍትሐዊና ዓለም አቀፍ አሰላለፍን የያዘው የብሪክስ መስመር 32 በመቶ የሚሆነውን የዓለም ኢኮኖሚ የምርት ጥቅል በእጃቸው ያደረጉ ኃያላን ሀገራት የሚገኙበት ቡድን ነው።

ቡድኑ የራሱ የሆነ የልማት ባንክ አቋቁሟል። ዓለም አቀፍ ተደማጭነትና በጎ ተፅዕኖ ያተረፈው ስብስብ ጠቀሜታውን ባስተዋሉ ሀገራት ዓይኖች ፈጥኖ መግባት ከጀመረ ቆይቷል። እንዲህ መሆኑ ከዓመታት በፊት የዓለም ኢኮኖሚን ከሚዘውሩት ምዕራባውያን ላይ የተተከሉ ዓይኖች እንዲነሱ አስገድዷል።

የቡድን አባላቱን ሰፊና ጠንካራ ዕቅድ በግልጽ የተረዱ ሌሎች ሀገራት እነሱን የመቀላቀል ፍላጎት እያሳዩ ነው። በአሁኑ ጊዜም ከአርባ በላይ ሀገራት የአባልነት ጥያቄን አቅርበዋል። ሀገራችን ኢትዮጵያም ብሪክስን ለመቀላቀል ፍላጎት ካላቸው ሀገራት መካከል አንዷ ሆናለች። ፍላጎቷን በተግባር ለማሳየትም የአባልነት ጥያቄ አቅርባ ተሳክቶላታል። ይህን አስመልክቶ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሞችና ፍላጎቷን ከሚያስከብሩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የመሥራት ጽኑ ፍላጎት አላት።

ባለፈው ዓመት በደቡብ አፍሪካ በተካሄደው አስራ አምስተኛው የፈጣን አዳጊ ሀገራት ጉባኤ ላይ ሀገራችን ተሳታፊ ነበረች። በዚህ ቆይታዋም ኢትዮጵያ በአባልነት እንድትቀጥል ይሁንታውን አግኝታለች። ሀገራችን ብሪክስን የመቀላቀሏ እንድምታ ውጤቱ መልካም እንደሚሆን ታምኖበታል።

ኢትዮጵያ በዚህ ውሕደቷ በየግዜው በምታደርጋቸው የኢኮኖሚ ለውጦችና አዳዲስ እንቅሰቃሴዎች መሠረቱን የሚያጸና ግንብ ይኖራታል። ይህ እውነታም ለሀገራችን የዲፕሎማሲው ድል ማስመስከሪያና ዋንኛ ማሳያ ነው። የሚሉ በርካቶች ናቸው። ብሪክስን ለመቀላቀል ፍላጎት ካላቸውና ጥያቄውን ካቀረቡ ከአርባ በላይ ሀገራት ስድስቱ ብቻ በመመዘኛ ተለይተው ተመርጠዋል። ከነዚህ መሐል ሀገራችን አንዷና ዋንኛዋ መሆኗ የዲፕሎማሲውን ፈጣን ርምጃ በገሐድ ያሳየ ምስክርነት ነው።

ለዲፕሎማሲው ግንኙነት ቅርበት ያላቸው ምሑራን እንደሚሉት ብሪክስን ለመቀላቀል በነበረው ጥረት ከእያንዳንዱ አባል ሀገራት ጋር በመገናኘት ጥበብና ብቃት የተመላበት ድል ለማስመዝገብ ተችሏል። በዚህም ሀገራቱ በኢትዮጵያ ማንነትና ወቅታዊ ቁመና ላይ ጽኑ አመኔታ ኖሯቸው በአባልነት እንዲመርጧት ምክንያት ሆኗል። ሀገራችን በዚህ የድል ጎዳና ላይ ለመቆም የተጓዘችባቸው መንገዶች ግን አልጋ በአልጋ አልነበሩም። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ይህ ልፋትና የበዛ ጥረት የተጀመረው ከዛሬ አስራ አራት ዓመታት በፊት ነበር።

ሀገራችን ከሌሎች ሀገራት ይበልጥ ለምርጫ እንድትታጭ ከሆነችባቸው ምክንያቶች አንዱ ለዘመናት በቅኝ ያለመገዛቷና ነፃነቷን አስከብራ የመኖሯ ሐቅ ነው። ከጥንት እስከዛሬ የዓለም አቀፍና አሕጉራዊ ዲፕሎማቶች መገኛና መቀመጫ የመሆኗ እውነትም ምርጫውና አመኔታው እንዲጣልባት ምክንያት ነበር። በበርካታ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ በመሪነት ሚና የነበራት ድርሻም የተለየ ግምት አግኝቷል።

ኢትዮጵያ በበርካታ እሾሃማ መንገዶች እያለፈችም ቢሆን ከሰሐራ በታች ካሉ ሀገራት በበለጠ ያስመዘገበችው ፈጣንና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከዓይን የሚገባና ለአርዓያነት የሚጠቀስ ነው። በነዚህና በሌሎች ተመራጭነት ብሪክስን መቀላቀሏ የዲፕሎማሲ አቅሟን የሚያሳድግና ተጨማሪ ገበያን የሚያሰፋ እንደሚሆን ጭምር ይታመናል። በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ላይ ለሚኖራት ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነትም ድርሻውን የጎላ ያደርገዋል።

ሰሞኑን ሞስኮ ላይ በተካሄደው የብሪክስ ቢዝነስ ፎረም ጉባኤ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቪዲዮ ባስላለፉት መልዕክት በኢትዮጵያ በፍጥነት እያደገ የሚገኘው ኢኮኖሚ ለብሪክስ አባላት አገራት ለኢንቨስትመንት፣ ኢኮኖሚያዊ ትብብርና ንግድ ታላቅ ዕድልን ይዞ መጥቷል። ኢትዮጵያ ያላት ዕምቅ የተፈጥሮና የግብርና ሀብት ሰፊውን የአፍሪካ ገበያና ከዚያም በላይ የሚፈልግ ነው። በካርጎ ጭነትና መንገደኞችን በማጓጓዝ ግንባር ቀደም የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድም ተጨማሪ ዕድል ሆኖ እንደሚያገለግል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በብሪክስ አባላት መካከል የጋራ ተጠቃሚነት መኖር ወሳኝነትን አንስተዋል። የዓለም አስተዳደራዊ መዋቅር ለታዳጊው ኢኮኖሚ ምላሽ ሰጪ እንዲሆንም በንቃት መሥራት ግድ እንደሚል አሳስበዋል። ዐቢይ (ዶ/ር) የብሪክስ አባል አገራት ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በቀጥታ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

በኢንቨስትመንቱ መሳተፍ ለሚፈልጉ በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በማዕድን፣ በታዳሽ ኃይል፣ በቴክኖሎጂና ቱሪዝም፣ ዘርፎች ትልቅ ዕድል መኖሩን በመግለጽ ሀገራቸው የ2025 የብሪክስ ኢኮኖሚ ትብብር ስትራቴጂ ስኬታማ እንዲሆን የበኩሏን ድርሻ እንደምትወጣ ጭምር መልዕክታቸውን አድርሰዋል።

ዜና

# የኮሪደር ልማቱ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማበልፀግ የመዲናዋን ዕድገት እያፋጠነ ይገኛል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኮሪደር ልማቱ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ከማበልፀግ ባለፈ የመዲናይቱን ሁሉን አቀፍ እድገት እያፋጠነ መሆኑን የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሣው (ዶ/ር ) ገለጹ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ቱሪዝም ሳምንትን በማስመልከት በአዲስ አበባ የሚገኙ የተለያዩ ሀገራት አምባሳደሮችና የዓለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮች የአዲስ አበባ ሙዚየምን፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያን፣ የሠላምና የወጣቶችን ፓርክንና ሌሎችንም በመዲናዋ የተሠሩ የልማት ሥራዎችን ጎብኝተዋል።

በዚሁ ወቅት የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሣው (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ የኮሪደር ልማቱ የመዲናይቱን ሁሉን አቀፍ እድገት በማፋጠን የአዲስ አበባ ከተማን ለመኖሪያ ምቹ ቦታ እንድትሆን እያገዘ ነው።

አዲስ አበባ በፈጣን እድገት ውስጥ ትገኛለች ያሉት



ሂሩት ካሣው (ዶ/ር)

የቢሮ ኃላፊዋ፤ ከተማዋ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እጅግ አስደናቂና አበረታች የሆነ ለውጥ እያስመዘገበች ሲሆን ከዓለም ዙሪያ የሚመጡ ጎብኚዎችን የምትስብ ከተማ እየሆነች ነው ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ እየተከናወነ የሚገኘውን የኮሪደር ልማት ጨምሮ በርካታ የልማት ሥራዎች ውጤታማ መሆናቸውን በመጥቀስ፤ የኮሪደር ልማቱ ለሁሉም ምቹና ተስማሚ የሆነች ከተማ ከመፍጠር ባለፈ ለዘላቂ የቱሪዝም እድገት ያለንን ቁርጠኝነት ያሳያል ሲሉ ተናግረዋል።

የቱሪዝም ሳምንት መከበሩ ባሕልን በመጠበቅ፣ ሠላምን በማስፈን እና በዜጎች መካከል አንድነትን በማጎልበት ረገድ ወሳኝ ሚና እንዳለው አንስተዋል።

ኢትዮጵያ ይህንን ራዕይ ለማሳካት ቱሪዝም የዜጎችን አንድነት፣ የጋራ መግባባትንና መከባበርን በማጠናከር ረገድ የራሱን ሚና እንዲጫወት ጥረት እያደረገች ነው ብለዋል፡፡

የዓለም የቱሪዝም ቀን በዓለም ለ45ኛ በኢትዮጵያ ለ37ኛ ጊዜ "ቱሪዝም ለሠላም፣ ሠላም ለቱሪዝም" በሚል መሪ ሃሳብ መከበሩን በመግለፅ፤ የአዲስ አበባ ቱሪዝም ሳምንት ከጥቅምት 16 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ሁነቶች እየተከበረ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

ጎብኝዎቹ በበኩላቸው አዲስ አበባ ከተማ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርጓትን የተለያዩ የልማት ሥራዎች እያከናወነች መሆኑን ገልጸው፤ ሁሉን አቀፍና በፈጣን የልማት ሥራዎቿ በሁለንተናዊ መልኩ ዘመናዊነትን እየተላበሰች እንደሆነ ተናግረዋል።

# የባሕር በርና ዓለም አቀፍ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጥቅምና ሉዓላዊነትን በተመለከተ ዝርዝር ጉዳዮችን ይዟል።

ዓለም አቀፍ የባሕር ሕጉ በአንቀጽ 69 የባሕር በር ባለቤት የሆኑ ሀገራት የባሕር በር ከሌላቸው ጋር እኩል የባሕር አካሉን ሃብት የመጠቀም መብት እንዳላቸው በግልጽ ያስረዳል።

የባሕር በር ሰፊ የሃብት ክምችትን የሚንቀሳቀስበት፣ አንድ ሀገር ከሌላው ጋር በቀጥታ የመርከብ ንግድ ግንኙነት የሚፈጥርበት ምስጢራዊ ዕቃዎችም ሆነ መሣሪያዎችን ለማስገባት የሚረዳ ተፈላጊ የአንድ ሀገር መተንፈሻ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በዚህ የተነሳ የባሕር በርን ለአንዳንድ ሀገሮች ብቻ የተፈቀደ ለሌሎች ደግሞ የተከለከለ በማስመሰል የሚቀርቡ ክርክሮች በአሁኑ ዘመን ላይ ተቀባይነት እያጡ ይገኛል።

ኢትዮጵያም ካላት የሕዝብ ቁጥርና የኢኮኖሚ ዕድገት አንጻር በጂቡቲ ወደብ ብቻ መጠቀም እንደሌለባት ገልጸ፤ ተጨማሪ ወደቦች እንደሚያስፈልጓት ማሳወቋ የሚታወስ ነው። ለመሆኑ ዓለም አቀፍ የባሕር በር አጠቃቀም ሕጎችና መርሆዎች ምን ይላሉ ጉዳዩስ ከሀገሪቷ ሁኔታዎች ጋር ምን ዝምድና ይኖራቸዋል በሚሉ ሃሳቦች ላይ የዘርፉ ባለሙያዎች ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የሕግና የአስተዳደር መምህሩ አሮን ደጎል፤ በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት የባሕር በር ብቻ ሳይሆን ሌሎች የኢኮኖሚ ጥቅም ሊያስገኙ የሚችሉ ነገሮች ካሉም ወደብ ያላቸው ሀገራት የእኔ ብቻ ነው ብሎ መጠቀም ብቻ ሳይሆን በእኩል ደረጃ የማስጠቀም ግዴታም ተጥሎባቸዋል ይላሉ።

በተመድ የዓለም አቀፍ ሕግ አንቀጽ 31 ላይ እንደተመላከተውም የአንድን ሀገር ሰንደቅ ዓላማ የሚያውለበልቡ መርከቦች በባለወደብ ሀገራት በኩል ሲያልፉ ሀገራቱ በእኩል ደረጃ መርከቦቹን የማስተናገድ ግዴታ እንዳለባቸውም ግዳጅ ያስቀምጣል ሲሉም ያነሳሉ።

እ.አ.አ. በ1958 የወጣው የጄኔቫ ስምምነት አንቀጽ 03 ወደብ የሌላቸው ሃገራት፣ የባሕሩን አካል የመጠቀም ዕድሉ ካላቸው ሀገራት ጋር በመነጋገር እንዲጠቀሙ መደረግ እንዳለበትም እንደሚደነግግም ነው የሚገልጹት።

እ.አ.አ. በ1965 በተፈረመ ዓለም አቀፍ ስምምነት ደግሞ ወደብ ወይንም የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት ምንም አይነት የባሕር በር ሊያገኙ አይገባም የሚል ፍጹም የሆነ ክልከላ መኖር እንደሌለበትም ያስቀምጣል።

በመሆኑም ሶማሊያ፣ ፑንት ላንድ፣ ኤርትራ፣ ጂቡቲ፣ ሱዳን በታሪክ አጋጣሚ ወይም በተፈጥሮም ቢሆን የባሕር በር ባለቤቶች ሆነዋል፤ ኢትዮጵያ ደግሞ ተጠቃሚ እንድትሆን ከእነዚህ ሀገራት ጋር ስምምነት ውስጥ መግባት እንዳለባት ይጠቁማሉ።

ስምምነት ላይ ተደርሶም ምናልባት በስምምነቱ አፈጻጸም፣ ይዘት፣ አተረጓጎም ላይ አለመግባባት ከተነሳ ወይም ደግሞ እኛ አንስማማም፣ ወደብ አንሰጥም ወይም በባሕር በር ኢትዮጵያ እንድትጠቀም አናደርግም ካሉ ደግሞ ሀገራቱ ዓለም አቀፍ ሕግ መጣሳቸው አይቀርም ይላሉ።

በዓለም አቀፍ ሕጎች መሠረትም የባሕር አካላትን በሚመለከት ወደብ ያላቸው ሀገራት ግዴታቸውን ካልተወጡ ወደፍርድ ቤት ይመጣሉ። ጉዳዩንም ወደስምምነት ኮሚሽን ወይንም ዓለም አቀፍ ልዩ ፍርድ ቤት (INTERNATIONAL TRIBUNAL) አምጥቶ ማሸነፍ የሚቻልበት ዕድልም እንዳለ ነው ያመላከቱት።

ስምምነት ካለ መልካም ነው፤ ስምምነት ከሌለና ባለወደብ ሀገራት ግዴታችንን አንወጣም አይነት እምቢተኝነትን ካሳዩ ደግሞ በሕጉ መሠረት ወደዓለም አቀፍ የፍትሕ ተቋማት ሄዶ መብትን ማስከበር እንደሚቻል ይጠቁማሉ።

ሕጋዊ መንገድን ከመጠቀም ውጭ ግን የማስገደድ፣ የጦርነትና መሰል መንገዶችን ዓለም አቀፉ ስምምነት አይደግፈውም፤ አመክንዮም የለውም፤ ይህንንም ኢትዮጵያውያን ይረዳሉ ሲሉ ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል።

የባሕር በር ጥያቄ ማንሳት የመርሕ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን መብትም ጭምር ነው የሚሉት መምህር አሮን፤ ዓለም አቀፉ የሕግ ማዕቀፍ፣ የ1982 የተባበሩት መንግሥታት ስምምነት፣ የጄኔቫ ስምምነት የኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ደጋፊ ሕጎችም የባሕር በር ተጠቃሚነትን የሚያግዙ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያም በባሕር በር ጉዳይ እንደሀገር ያነሳችው የመብት ጥያቄ ነው። መብትን መጠየቅ በሕግ የሚያስጠይቅ ባለመሆኑ የግዴታው ባለቤት የሆነው ሌላኛው አካል የባሕር በር ተጠቃሚነት መብቱን ማክበር አለበት ይላሉ።

ምናልባት በባሕርና በወደብ አጠቃቀም አለመግባባቶች ቢያጋጥሙ ግጭቶች ወይም አለመግባባቶች ቢያጋጥሙ የሚፈታበት ሕግ ስላለ በጎረቤት ሀገራት የሚነሱ ስጋቶች አላስፈላጊ መሆናቸውን ያነሳሉ።

የ1982ቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የባሕር ሕግን የሚደነግገው ስምምነት አንቀጽ 279 እና ተከታዮቹ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ማስቀመጡን ይገልጻሉ። ለአብነት አንዱ ዘዴ በሚኖረው የእርቅና የስምምነት ኮሚሽን መሠረት ይፈታል። በዚህ ካልተፈታ በየደረጃው እየታየ እስከ ዓለም አቀፉ የፍትሕ አካል የሚሄድበት ሁኔታ ይኖራል። ወይንም ለዚህ ዓላማ ብቻ የፍርድ ውሳኔ የሚሰጡ አካላት ሊቋቋሙም ይችላሉ። በተቻለ መጠን ከሀገራት ጋር በሕግ፣ በስምምነት እንዲፈቱ የሚያበረታታ ነው ይላሉ።

የስምምነት ኮሚሽኑ መጨረሻ ላይ የሚያቀርበው ሪፖርት ገዢ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን መመሪያ አሊያም አቅጣጫ ያስቀምጣል። ነገር ግን ወደጦርነትና ግጭት የሚሄድበት አግባብ እንደማይኖር ሕጉ ይደነግጋል ሲሉ ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር የተፈራረመችው አይነት የወደብ ተጠቃሚነትን የሚያሰፋ ስምምነት ከሌሎች ሀገራት ጋርም መቀጠል እንዳለበት የተናገሩት ደግሞ የምጣኔ ሀብት ምሑሩ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) ናቸው።

የመግባቢያ ሥምምነቱ የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄ ሊመልስ የሚችል ኩነት ነው፤ ዓለም አቀፍ ሕግጋት የሚደግፉትና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ላይ መሠረት ያደረገ በመሆኑ ኢትዮጵያን በተመድ ጉባኤዎች ላይም በስፋት አንስታ ልትጠይቅበት የምትችልበት አግባብ መኖሩን ይጠቁማሉ።

ኢትዮጵያ እራሷ የምታለማው ወደብ ሲኖራት፣ የሸቀጥ ዕቃዎችን ወደ ውጭ ለመላክም ሆነ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ሰፊ አማራጭ ያስገኝላታል። ይህም ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሶማሌላንድም የገቢ ምንጭ ይኖረዋል ይላሉ።

ሥምምነቱ ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ በሠላምና ደኅንነት ዘርፍ ያላትን አዎንታዊ ሚና ይበልጥ እንድታጠናክርም ዕድል ይሰጣታል፤ በመሆኑም ዓለም አቀፍ ሕግጋትን በማጣቀስና ሀገራትን በዲፕሎማሲ በማግባባት ቀጣይነት እንዲኖረው መሥራት ይገባል ሲሉ ያስረዳሉ።

# “ከግማሽ ምዕተ ዓመት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር አንዋር ኢብራሂም ብሎም የማሌዢያ ሕዝብ እና መንግሥት በቆይታችን ለሰጣችሁን ደማቅ አቀባበል እና ፍቅር እናመሰግናለን ብለዋል።

ትብብራችንን ትኩረታቸውን በግብርና፣ ማዕድን፣ ማኑፋክቸሪንግ እና ታዳሽ ኃይል ላይ ባደረጉ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ዘርፎች ብሎም ሰፊ አድማስ ባላቸው ሌሎች ቁልፍ ሥራዎች ላይ ለማጠናከር ተስማምተናል በማለትም ገልጸዋል።

የማሌዢያ ጠቅላይ ሚኒስትር አንዋር ኢብራሂም በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ አሕጉር ከሚገኙ ሀገራት መካከል ዋነኛ የሀገራቸው አጋር መሆኗን አስታውቀዋል።

ማሌዢያ ከኢትዮጵያ የምትማራቸው በርካታ ጉዳዮች በመኖራቸው ግንኙነቱን በማጠናከር እንሠራለን ሲሉ ገልጸዋል።

ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጋር ወደ ማሌዥያ ያቀናው የኢትዮጵያ ልዑክ ከሀገሪቱ የንግድ ማኅበረሰብ አባላት ጋር ተወያይቷል።

ልዑኩ በኢትዮጵያ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና ማቀነባበሪያ፣ በፋርማሲዩቲካል፣ በጨርቃጨርቅ፣ በማዕድን እና ኮንስትራክሽን ዘርፎች ያሉ ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጮችን በተመለከተ ለንግድ ማኅበረሰቡ ማብራሪያ ሰጥቷል።



አብርሃም በላይ (ዶ/ር)

# የ46 ሚሊዮን ዶላር ፕሮጀክቶቹ የመስኖ ልማትን ለማሳደግ ዓይነተኛ ሚና አላቸው

**ማርቆስ በላይ**

ቢሾፍቱ፡- በ46 ሚሊዮን ዶላር ወጪ በሦስት ክልሎች ውስጥ እየተገነቡ ፕሮጀክቶች የመስኖ ልማትን ለማሳደግ አይነተኛ ሚና እንዳላቸው የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ምርታማነት ማሳደጊያና የሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮጀክት ላይ ትናንትና ውይይት ተካሂዷል።

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር አብርሃም በላይ (ዶ/ር) በውይይቱ ወቅት እንደገለጹት፤ ጊዳቦ፣ በለጪትና ጣባ የመስኖ ፕሮጀክቶች በኦሮሚያ፣ በአማራና ሲዳማ ክልሎች እየተገነቡ ይገኛል።

ፕሮጀክቶቹ ግብርናን ለማዘመን፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠርና ከኢንዱስትሪው ጋር የምርት ትስስር ለመፍጠር አይነተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ጠቁመዋል።

የተለያዩ ማኅበረሰቦችን የሚያስተሳስሩት ፕሮጀክቶቹ በተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች አካባቢ የመስኖ ግድብ ፕሮጀክቶችን ግንባታ በማስፋፋት የግብርና ምርትን ምርታማነት ለማሳደግ ያለሙ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

ፕሮጀክቶቹ በተለይም የተረጋጋ የንግድ ሥርዓትን ለመፍጠር ከኢንዱስትሪው ጋር ትስስር እንዲኖር የሚያስችሉ ናቸው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በተጨማሪ ለወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ዘመናዊ ግብርናን ለማሳደግ ይረዳሉ ብለዋል።

በአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች አካባቢ የአርሶ አደሮችንና ወጣቶችን የግብርና ምርታማነት ማሳደግ የሚያስችሉ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ ለልማቱ መፋጠን አስፈላጊ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ጌታሰው መኮንን በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቶቹ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች መስኖን በማዘመን ወንዞችንና ግድቦችን ተከትሎ ወጣቶችን ወደ ሥራ ለማሠማራት ያለሙ መሆናቸውን አንስተዋል።

በፕሮጀክቱ አማካኝነት ሦስት ሺህ ወጣቶች ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በሁለት ዓመታት ውስጥ ግንባታውን በማጠናቀቅ ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግ አመላክተዋል።

በሦስቱ ክልሎች ተግባራዊ የሚደረጉት ፕሮጀክቶች አጠቃላይ ወጪ 46 ሚሊዮን ዶላር መሆኑን ለወጣቶች የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ የግብርናውን ዘርፍ ከኢንዱስትሪው ጋር በማስተሳሰር የግብዓት አቅርቦትን የሚያሳድጉ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በፕሮጀክቶቹ ከገንዘብ ሚኒስቴርና ልማት ባንክ በኩል ለወጣቶች የቴክኖሎጂና ለእርሻ ግብዓት የሚሆኑ መሣሪያዎች ግዥ የሚውል ድጋፍ እንደሚደረግ አመላክተዋል።

ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የሚውሉ የሞተር ሳይክልና ተሽከርካሪዎች ለክልሎችና ለፌዴራል የፕሮጀክቱ አስፈጻሚዎች ተበርክቷል።

በመድረኩ የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስትር አብርሃም በላይ (ዶ/ር)፣ የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)፣ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚልን ጨምሮ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

# አለመማር ያልገደባቸው ችግር ፈቺው የፈጠራ ሰው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ የምርምር ስራዎችን ለማከናወን ብዙውን ጊዜ መማር መሰልጠን አልያም በተሻለ የኑሮ ደረጃ መገኘት ይጠይቃል። በዚህ ሂደት ውስጥ አልፎ ከምርምር የተገኙ የተመሰከረላቸው ጠቃሚ ውጤቶችን በነጻ ለተጠቃሚ ማበርከት ደግሞ ለሀገር ያለን ቀናኢነት የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን ልዩ የሕዝብና የሀገር ፍቅርንም የሚጠይቅ ነው። ይህንን ለማድረግ የሚታደሉት ታዲያ ጥቂቶች ብቻ ናቸው። የሚገኘው ጥቅም ደግሞ ብዙሃኑን ሕዝብ ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን፤ ለሰሪውም ሆነ ለተመልካች የሚፈጥረው ደስታ እጥፍ ድርብ ይሆናል።


እንዲህ አይነት የበጎነት አገልግሎት ተግባራት በወቅቱ ከሚሰጡት ጥቅም ባለፈ ለትውልዱም የሚያስተላልፉት መልእክት ይኖራል። ማለትም አንድ ግለሰብ ለሀገርና ለሕዝብ የሠራቸውን አበርክቶዎች በማየት ነገ እኛም እንዲህ ብናደርግ ምስጋናና ፍቅርን እናገኛለን የሚል ትውልድ መፈጠሩ አይቀርም። የዛሬው የሕይወት አምድ እንግዳችን አቶ ተገኑ አየለ ይባላሉ። በመደበኛው የትምህርት ሂደት እዚህ ግባ የሚባል ደረጃ ባይኖራቸውም ከራሳቸው አልፈው በርካቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ስራ ለመስራት የቻሉ ናቸው። እኚህ አባት ዛሬም ድረስ በእርጅና ዘመናቸው ላይ ሆነው የልፋታቸውን ውጤት ለሌሎች ለማዳረስ በራቸውን ክፍት አድርገው በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ።

**ውልደትና እድገት ፤**

አቶ ተገኑ አየለ የተወለዱት በ1941 ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ዞን ደራ ወረዳ ልዩ ስሙ ጉንዶ መስቀል በሚባል አካባቢ ወሬ ሁላ በተባለች መንደር ነው። የአቶ ተገኑ ቤተሰቦች በዘመናቸው ባላባት የሚባሉ የተትረፈረፈ ሀብት ያላቸው አዛዦችም ነበሩ። እናታቸው ወይዘሮ እናኑ አለሙ ገና የሶስት ዓመት ልጅ እያሉ ሳይታሰብ አይናቸው የጠፋ ቢሆንም፤ የባላባት ልጅ በመሆናቸው በወቅቱ ትዳር እንዲመሰርቱ ተደርገው ይኖሩ ነበር። በዘመድ አዝማድ በተከበበ መንደር ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ይኖሩ የነበሩት የአቶ ተገኑ ቤተሰቦች በአንድ ጥሩ ያልሆነ ወቅት የቤተሰቡን አቋም የሚያናጋ አጋጣሚ ተፈጠረ። በ1953 ዓ.ም በአካባቢው በስፋት ተከስቶ የነበረው የወባ በሽታ የአቶ ተገኑን አባት ጨምሮ በርካታ ቤተሰባቸውን ለሞት ዳረጋቸው።

በዚያ ጊዜ አቶ ተገኑ ቤተሰብ ለመንከባከብ የሚያበቃቸው አቅም ባይኖርም ትልልቆቹ ሰዎች በሙሉ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው እናታቸውን እና ታናናሽ ወንድሞቻቸውን እና እህቶቻቸውን የመጠበቁ ኃላፊነት በእርሳቸው ጫንቃ ላይ ወደቀ። የተፈጠረውን ነገር በፀጋ የተቀበሉት አቶ ተገኑ ደከመኝና ሰለቸኝ ሳይሉ ማየት የተሳናቸውን እናታቸውን ጨምሮ መላውን ቤተሰብ የመንከባከበቡን ኃላፊነት መወጣት ቀጠሉ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ፤ አንድ ቀን የከትክታ እንጨት ሲፈልጡ የተፈናጠረች የእንጨት ስንጣሪ የቀኝ አይናቸው ውስጥ ገባች። በወቅቱ በአካባቢው በቂ ሕክምና ባለመኖሩ እና ቤተሰባቸውንም ትተው መንቀሳቀስ ስላልፈለጉ ያቺን ስንጣሪ በአይናቸው ውስጥ እንደገባች ለረዥም ዓመት አቆይዋት። ከዚህ በኋላ ነገሮች እየተባባሱ ሲመጡ ከአንድ ጓደኛቸው ጋር በመሆን በ1959 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ወሰኑ።

በወቅቱ በቂ የሚታረስ መሬት ስለነበር እናታቸውን እንዲንከባከቧቸው ለአራት ወንድምና እህቶቻቸው ትተው ወደ አዲስ አበባ ያቀናሉ። አዲስ አበባም እንደ ደረሱ እርሳቸው በቅርበት የሚያውቁትና ያዘጋጁት የኔ የሚሉት ማረፊያ የሚሰጥ የሚያስጠጋ ዘመድ ስላልነበራቸው፤ መዳረሻቸው ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ አብሯቸው ከመጣው ጓደኛቸው ዘመድ ቤት ነበር። እዛም ተቀምጠው ለተወሰነ ጊዜ የቀን ሥራና ሌሎች ስራዎችንም እየሰሩ ቆዩ። ከጊዜ በኋላ ችግራቸውን የተገነዘበ በቅርበት የሚያውቃቸው አንድ የበግ ነጋዴ በአንድ ግለሰብ ቤት



**አቶ ተገኑ አየለ**

እንዲቀጠሩ ሁኔታዎችን አመቻቸላው። ጥያቄውን የተቀበሉት አቶ ተገኑም እዚያ ቤት ለስራ በገቡበት አዲሱ ቤት ጥበቃን ጨምሮ የተለያዩ ስራዎችን እያከናወኑ ለዓመታት ሲያገለግሉ ቆዩ።

በ1960 ዓ.ም ግን በሕይወታቸው አዲስ ምእራፍ የሚጀምርበት አጋጣሚ ተፈጠረ። በቤታቸው ሲያሰሯቸው የነበሩት ግለሰብ አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የሚሠሩ መሀንዲስ ነበሩ። እናም የአቶ ተገኑን ቅልጥፍና እና ታዛዥነት በማየት እርሳቸው የሚሰሩበት ተቋም ውስጥ እንዲቀጠሩ አደረጓቸው። አቶ ተገኑ ሥራቸውን የጀመሩት በቀን ሰራተኝነት የፓንፕ ኦፕሬተር በመሆን ነበር። የሥራ ቦታቸው ደግሞ እዛው ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ በሚገኝ ትልቅ የውሃ ማጠራቀሚያ ግቢ ውስጥ ነው። በዚህ ሁኔታ ከቆዩ በኋላ የደርግ መንግስት በመጣበት ወቅት መንግስት ለበርካታ ተቋማት ያስተላለፈው ውሳኔ እርሳቸው የሚሰሩበት መስሪያ ቤትም ይደርስና ቋሚ ሰራተኛ ለመሆን በቁ። ከዚህ በኋላ በተለያዩ ጊዜያት በቆጣሪ ምርመራ ክፍል፤ በቴክኒሺያንነት፤ በሲኒየር ቴክኒሺያንነት ደረጃ ለመሥራት በቅተዋል። በእነዚህ ጊዜያትም ቀልጣፋ ስለነበሩና የተሻለ አፈፃፀምም ስለነበራቸው በአዲስ አበባ ዋና ዋና በሚባሉት አካባቢዎች ለአስቸኳይ ስራ ሰራተኛ ሲፈለግ ከሚመሩት መካከል ሆነው ይመደቡ የነበሩትም እርሳቸው ነበሩ። አቶ ተገኑ ብሔራዊ ቤተ መንግስት፤ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግስት፤ ፓርላማ፤ ጥይት ቤት፤ አፍሪካ ሕብረት፤ አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት እና ሌሎችም አካባቢዎች ላይ ይሠሩ ነበር።

**የቤተሰብ ሁኔታ**

አቶ ተገኑ ትዳር መስርተው አዲስ ሕይወት መኖር የጀመሩት በ1964 ዓ.ም ነው። ዛሬ ድረስ የትዳር አጋራቸው የሆኑትንና «እዚህ ለመድረሴ ምክንያት ነች» የሚሏቸውን ባለቤታቸውን ያገኙበትንም አጋጣሚ እንዲህ ያስታውሱታል። «እኖር የነበረው አሁን ያለሁበት አካባቢ በቤት ኪራይ ነበር፤ ከባለቤቴ ወይዘሮ የሻረግ ገብረህይወት ጋርም የተገናኘነው እዚሁ አካባቢ ነው። ትውልዷ አንኮበር አካበቢ ሲሆን፤ በወቅቱ እኛው ሰፈር ሰው ቤት ተቀጥራ ትሰራ ነበር። ግንኙነታችን የጀመረውም በዚሁ አጋጣሚ ነው። ካየኋትና መግባባት ከጀመርን በኋላ እራሴው ጥያቄ አቅርቤ ፈቃደኛ በመሆኗ ወዲያው ትዳር ለመመስረት በቃን። ባለቤቴ ጥሩ ጸባይ ያላት ብቻ ሳትሆን ጓደኛም ሰው ነበረች። ከተጋባን ጊዜ ጀምሮ አንድ ቀን ችግር የሚባል ነገር ገጥሞኝ አያውቅም።

በ1975 ዓ.ም ቦታ ተመርተን ቤት ሰርተናል። ላለፉት አርባ ዓመታትም የራሴን መኪና ገዝቼ ሳሽከረክር ቆይቻለሁ። ባለቤቴ ለኔም ጥሩ ሚስት፤ ለልጆቼም ጥሩ እናት ነች። በትዳር ዘመናችን ሰባት ልጆችን ወልደን አስራ ስድስት የልጅ ልጆችንም ለማየት በቅተናል። እሷ በሁሉም ነገር ከጎኔ ትቆምና ታበረታታኝ ስለነበር አቅጄ ያላሳካሁት ነገር አልነበረም። ልጆችን በማሳደግ ረገድም የተዋጣላት ነበረች። ልጆቻችን ጥሩ ስነ ምግባር ያላቸው ስራ የሚወዱና ታዛዥ ናቸው። ለዚህ ደግሞ እርሷ ብዙውን ሥራ ሰርታለች። ዛሬም ድረስ የሚሰማኝ የእናቴ ምትክ እንደሆነች ነው » ይላሉ።

**የምርምር አበርክቶ**

አቶ ተገኑ በተቀጠሩበት መስሪያ ቤት ጠንካራና ጎበዝ ከሚባሉት ቀዳሚ ሰራተኞች መካከል ለመሆን በቅተዋል። በቆጣሪ የምርመራ ክፍል፤ በቴክኒሺያንነትና በኮሌጅ ምርመራ ዘርፍ በሲኒየር ቴክኒሺያንነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ይህም ሆኖ አቶ ተገኑ የሁኔታዎች አለመመቻቸትም ሆነ የአንድ አይናቸው ጉዳት ለመማር ለማወቅ የነበራቸውን ፍላጎት አላገደውም። የነበሩት ሁኔታዎች ምቹ ባይሆኑም ያለውን አጋጣሚ በመጠቀም ሚያዚያ 23 መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ እስከ ስምንተኛ ክፍል ለመማር ችለዋል። አቶ ተገኑ ወደ ምርምር ስራ የመራቸውንና በተለያዩ ጊዜያት እስከ መሸለም ያ ደረሰ ውጤት ያስገኘላቸውን ሥራ የጀመሩበትን አጋጣሚ እንዲህ ያስታውሱታል።

«አንድ ቀን በቀድሞው የፍትህ ሚኒስቴር ሕንጻ አካባቢ ውሃ እየፈሰሰ እንደሆነ መረጃ ይደርሰንና ለመጠገን እንቀሳቀሳለን። እዛ ደርሰንም ችግሩ የተፈጠረበትን ቦታ ለመለየት ያደረግነው የተለያየ ሙከራ እንደሌላው ጊዜ በቀላሉ ውጤታማ ሳይሆን ቀረ። ከብዙ ልፋት በኋላ ከውጪ ሀገር ጃፓን ተምረው የመጡ ባለሙያዎች እኛ በወቅቱ እንድንጠቀምባቸው የማይፈቀዱልንን «ሳውንዲንግ ባር» እና «ቦሪንግ ባር» በመባል የሚታወቁ መሳሪያዎችን በመጠቀም ችግሩን ይለዩታል። ለካስ ቧንቧው የተሰበረው እዛ አካባቢ ሳይሆን በርቀት ቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ ነበር። ከዚያ በኋላ ባለሙያዎቹ የተጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ምንድን ናቸው? ብለን ስናጣራ «ሳውንዲንግ ባር» በተለያዩ ምክንያቶች የቧንቧ መስመር ተበላሽቶ ውሃ እየፈሰሰ ከሆነ ያለበትን ቦታ በድምፅ ለመለየት የሚያስችል ነው። ሌላኛው « ቦሪንግ ባር » ደግሞ ተመሳሳይ ችግር በአስፋልት እና ኮንክሪት ንጣፍ ባለባቸው ቦታዎች ላይ ሲደርስ አስፋልቱ ሳይቆፈር በመሬት ውስጥ እርጥበትን መነሻ በማድረግ ችግሩ ያለበት ቦታ የሚለይበት መሳሪያ መሆኑን ስረዳ እነዚህን መሳሪዎች ለማግኘት ወይም ለመስራት ተመኘሁ።

ከዚያ በኋላ ባሉት ጊዜያትም በየእለት ከእለት ሥራችን እነዚህን መሳሪያዎች ለመጠቀም የምንፈልግ ቢሆንም እንከለከል ስለነበር ማግኘት ሳንችል ለረዥም ግዜ ለመቆየት ተገደድን። በእነዚያ ጊዜያትም ስራችንን እናከናውን የነበረው አካባቢውን በመቆፈር በተለመደው አድካሚና ብዙ ጊዜ የሚጠይቅ ብዙ ኪሳራም የሚያስከትል አሰራር ነበር። በዚህ አጋጣሚ እነዚያ መሳሪያዎች እንዲኖሩኝ ነገሩን ተከታትዬ ለማወቅ መጣር ጀመርኩ። ነገር ግን መሳሪያዎቹ ከውጪ የመጡና ውድ በመሆናቸው ይበላሻሉ በሚል

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

**“ሳውንዲንግ ባር” በተለያዩ ምክንያቶች የቧንቧ መስመር ተበላሽቶ ውሃ እየፈሰሰ ከሆነ ያለበትን ቦታ በድምፅ ለመለየት የሚያስችል ነው**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# አለመማር ያልገደባቸው...

ከገጽ 6 የዞረ

ሰበብ ከባለሙያዎች ውጪ ማንም እንዲጠቀምባቸውም ሆነ እንዲነካቸው አይፈቀድም ነበር።» ይላሉ።

ያ ዘመን በአንድ ወገን መላው የከተማ ነዋሪ በቂ ውሃ የሚያገኝበት ጊዜ አልነበረም። በአንፃሩ ደግሞ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች በግለሰቦች ግቢ ውስጥም ሆነ በመንገድ ላይ እዚህም እዛም እየፈሰሰ የሚውል ከፍተኛ መጠን ያለው ውሃ ነበር። ይህ ነገር ደግሞ አቶ ተገኑን በእጅጉ ያበሳጫቸው ያሳስባቸውም ነበር። ውሃው በመንገድ ላይ የሚፈስ ቢሆንም እንደ ሀገር የሚያስከትለው ችግር አለ። የሚፈሰው ደግሞ በግለሰቦች ቤት ሲሆን ያልተጠቀሙበትን እንዲከፍሉ ከማድረግ ባሻገር ባለቤቶችን ከተከራይ እና ከውሃ ፍሳሽ ሰራተኞች ጋር ተገቢ ወዳልሆነ እሰጥ አገባ ውስጥ ሲከታቸው በተደጋጋሚ ይስተዋላል። ከሁሉም በላይ ደግሞ አንድ ቦታ የውሃው መስመር ተበላሽቶ ውሃ ወደውጪ መፍሰስ ጀመረ ማለት ውሃ በጠፋበት ወይንም በተቋረጠበት ወቅት መስመሩ በአካባቢው ያለውን የተበከለ ቆሻሻ ውሃ ወደመስመሩ ስቦ ያስገባዋል። ይህ ከግለሰብ አልፎ ለማህበረሰብ ጤና ጠንቅ የሚሆን ነው። በዚህም የተነሳ አቶ ተገኑ የመሳሪያዎቹ በስፋት መመረትና ወደ ስራ መግባት የግድ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ደረስኩ። ይላሉ።

አቶ ተገኑ ይህን ሀሳባቸውን ይዘው ባለበት ወቅት አንድ ቀን የቅርብ አለቃቸው እቃዎቹን መኪና ውስጥ ትቶ ሲሄድ፤ አጋጣሚውን በመጠቀም በደንብ አገላብጠው እያንቀሳቀሱ የመመልከቱን እድል ያገኛሉ። በወቅቱ የተረዱትና ለራሳቸው የነገሩት ነገር ቢኖር መሳሪያዎቹን ራሳቸው መስራት እንደሚችሉ ነበር። በዚህም መሰረት ብዙም ጊዜ ሳይሰጡ እቅዳቸውን ለማሳካት መንቀሳቀስ ይጀምራሉ። በዚህም በቅርብ በአካባቢያቸው ያገኟቸውን እንደ ፌሮዎች ያሉ ብረቶችን በመሰብሰብ መስራት ይጀምራሉ። በዚህ እንቅስቀሴ ሊሳካ እንደሚችል የሚያመላክት የተወሰነ ውጤት ቢያገኙም አመሳስሎ የመስራቱ ነገር በፈለጉት መልኩ ሳይሳካለቸው ይቀራል።

ከተወሰነ ጊዜያት በኋላ የመጀመሪያ ስራቸው ያልተሳካው የብረቱ አይነት የተለየ መሆኑን በመረዳት ለዛ የሚሆን ብረት ለመፈለግ ወደ መርካቶ ሱማሌ ተራ ያቀናሉ። ከጥቂት ውጣ ውረድ በኋላ አላማቸውን ሊያሳካ የሚችል ብረት ለማግኘት ይበቃሉ። ይጠቅሙኛል ያሏቸውን ግብአቶች ሰብስበው በመሄድ ስራቸውን በድጋሚ እንዳዲስ ይጀምራሉ። ነገሩን በደንብ ተረድተውት ስለነበር ብዙም ሳይለፉ መሳሪያዎቹን ከውጪ ከመጡት ጋር አመሳስለው ለመስራት ይበቃሉ። በራሳቸው መስፈርትም መሳሪያዎቹን ሞክረው መስራታቸውን ያረጋግጣሉ። ቀጥለውም ከዚህ ቀደም በከፍተኛ ወጪ ወደ ሀገር ቤት የገቡት መሳሪያዎች በምን መስፈርት ተመርምረው ይሆን ወደ ሀገር ቤት የገቡት የሚል ጥያቄ በአእምሯቸው ይመጣል። ይህም ሆኖ እርሳቸው ያረጋገጡትን ነገር ብቻ ይዘው ምንም ነገር ለማድረግ ስላልፈቀዱ አማራጭ ያደረጉት ውጪ ሀገር በመሄድ ሰልጥነው የመጡ ባለሙያዎች ትክክለኛነቱን እንዲመረምሩላቸው መጠየቅ ነበር። ባለሙያዎቹም የተሰሩትን ነገሮች አቅማቸው በፈቀደ ፈትሸው የፈጠራ ስራው ትክክል መሆኑን እና ከውጪ ከመጣው ጋር ተመሳሳይ ስራ ሊሰራ የሚችል መሆኑን ያረጋግጣሉ።

አቶ ተገኑም እነዚህን ውጤቶች መነሻ በማድረግ መሳሪያዎቹን ወደመስሪያ ቤታቸው በመውሰድ በስጦታ ያበረክታሉ። የተቋሙ ኃላፊዎችና ሰራተኞች መሳሪያዎቹ መስራት የሚችሉ መሆናቸውን ቢያረጋግጡም፤ ነገሩ በሌላ ሶስተኛ ወገን መረጋገጥ ስላለበት ለጥራትና ደረጃዎች መዳቢ ባለስልጣን ደብዳቤ ይፅፉና ይልኳቸዋል። ጥራትና ደረጃዎች መዳቢ ባለስልጣን ግን የእዚህ አይነቱን መሳሪያ የሚመረምርበት ማሽን ስለሌለው እንደማይችል ያስታውቃል። እንደ ግለሰብ አቶ ተገኑ እየተገለገሉባቸው ቢሆንም መሳሪያዎቹ ግን ለዘጠኝ ዓመት ያክል እውቅናም ክልከላም ሳያገኙ በእንጥልጥል ይቆያሉ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ አቶ አሊ አብዶ የከተማዋ ከንቲባ ሆነው ከተሾሙ በኋላ ግን አዲስ ታሪክ የሚጀምርበት አጋጣሚ ይፈጠራል። ግምገማ መካሄድ ስለነበረበት ሁሉም ሰራተኛ የተሰበሰበበት



**አብዛኛው የውሃ መስመር ከውሃ መፍሰሻ ቦዮች ጋር አንድ ላይና የተቀራረበ መሆኑ የውሃ መስመሮችን ለመበከል ቅርብ ያደርጋቸዋል**

የውይይት መድረክ ሲካሄድ አቶ ተገኑ የሆነውን ነገር ሁሉ ለከንቲባው ያሰረዳሉ። ከንቲባውም ይህ ነገር ራሱ የመልካም አስተዳደር ክፍተት መኖሩን አመላካች እንደሆነ በመግለፅ ለቦርድ እንዲቀርብና በተገቢው ደረጃ ታይቶ ለጉዳዩ መልስ እንዲሰጥ ትእዛዝ ያስተላልፋሉ። በዚህም መሰረት ዘጠኝ ዓመት የተቀመጠው ጉዳይ በሶስት ወር ውስጥ ምላሽ ለማግኘት ይበቃል። በመልሱም መሳሪያዎቹ ከውጭ ሀገራት ከመጡት ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንደሆኑ በመግለፅ በብዛት ቢመረቱም ከውጪ የሚመጣውን ሊተኩ የሚችሉ መሆናቸው ማረጋገጫ ይሰጣቸዋል። አቶ ተገኑም መሳሪያዎቹ ተባዝተው በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በመላው ሀገሪቱ መዳረስ አለባቸው ብለው ስላሰቡ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ስራቸውን ያቀርባሉ። ሳይንስና ቴክኖሎጂም የተወሰነ ጊዜ በጥናትና ምርምር መሳሪያዎቹን ፈትሾ ችግር የሌለባቸው መሆናቸውን በማረጋገጥ እውቅና ይሰጧቸዋል።

ከዚህ በኋላ የአቶ ተገኑ የልፋት ውጤቶች ይፋ በመሆኑ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እና ሬዲዮ በተደጋጋሚ ይቀርቡ ነበር። ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ እውቅና እና አድናቆትን አስገኝቶላቸው ቆይቷል። በዚህም ደሴ ባቲ ጠቅላላ ሆስፒታል ተመሳሳይ ችግር ገጥሞት ለረዥም ዘመን ቆይቶ ነበር። በእርሳቸው በኩል የሆስፒታሉ ችግር ተቀረፈ። የሆስፒታሉ ባለቤትም በተሰራው ስራ በመደነቅ ከገንዘብ ክፍያ ባለፈ ሁለት ኩንታል ጤፍ በመስጠት አቶ ተገኑን እቤታቸው ድረስ ይመልሷቸዋል። በተመሳሰይ አዲስ አባባ ዋሪት ሕንፃ፤ ጌጅ ኮሌጅ፤ አገልግሎቱን አግኝተው ለአቶ ተገኑ የምስጋና ደብዳቤ ካበረከቱላቸው ተቋማት መካከል ይጠቀሳሉ።

## የጡረታ ሕይወት

አቶ ተገኑ በዚህ ሁኔታ በሞራል በመስሪያ ቤታቸው ሲሠሩ ቢቆዩም በ1996 ዓ.ም እርሳቸው ባይፈቅዱም የሕይወታቸውን መስመር የቀየረ አጋጣሚ ይፈጠራል። ወቅቱ መንግስት የትምህርት ማስረጃን መሰረት በማድረግ የሰራተኞች ድልድል ማድረግ የጀመረበት ጊዜ ነበር። ይህንንም ተከትሎ በአቶ ተገኑ ስር ይሰሩ የነበሩት ሰዎች የተሻለ የትምህርት ማስረጃ አላቸው ስለተባለ ሁሉም እንዲያድጉ ጥቂቶቹም የእርሳቸው ኃላፊ እንዲሆኑ ይደረጋል። ተቋሙም ኃላፊዎቹም ሆነ ሰራተኞቹ አቶ ተገኑ ትጉህ ሰራተኛ ብቻ ሳይሆኑ ራሳቸው የሰሯቸውን ስምንት መሳሪያዎች ያለምንም ክፍያ ለተቋሙ ያበረከቱ መሆናቸው እየታወቀ በድልድሉ ካሉበት ደረጃ ዝቅ እንዲሉ ይደረጋሉ። አንዳንዶችም የደረጃ እድገቱን አስመልክተው አቶ ተገኑን ተመራማሪው... ባለግኝቱ ... እያሉ ያሾፉባቸው ስለነበር እርሳቸውም መረበሽ ይጀምራሉ። በዚህም የተነሳ ግንቦት ሰላሳ ቀን 1996 ዓም በፈቃዳቸው ጡረታቸውን አስከብረው ስራቸውን ለመልቀቅ ይገደዳሉ።

አቶ ተገኑ በዚህ አይነት መገፋት ሊባል በሚችል ደረጃ ለሰላሳ አምስት ዓመታት ያህል ያገለገሉበትን መስሪያ ቤት በፈቃዳቸው ቢለቁም፤ ከስራቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ግን አልተቋረጠም ነበር። ምንም እንኳን ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር የገንዘብ ችግር ባይኖርባቸውም ብዙ የተመሰገኑበትን ስራቸውን በግላቸው መስራት ይጀምራሉ። ቦሌ መንገድ ወሎ ሰፈር አካባቢ «ተገኑ የውሃ ብክነት ምርመራ ድርጅት » የሚል በማቋቋምም ስራቸውን ይቀጥላሉ። በእነዚህ ጊዜያትም እርሳቸው ጋር እየቀረቡ የስራ እድል ከማግኘት ባለፈ እውቀት ለማግኘት የበቁ በርካታ ወጣቶች ነበሩ።

ይህ እንዳለ ሆኖ በተቋም ደረጃ እውቀትና ልምዴን ለትውልድ ማስተላለፍ አለብኝ ብለው የሚያምኑት አቶ ተገኑ የነጻ ስልጠና ለመስጠት የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ሲጠይቁ ቆይተዋል። ከእነዚህም መካከል ይሰሩበት ከነበረው ተቋም ውጪ የሚከተሉትን በደብዳቤ ጠይቀው ነበር። በወቅቱ የአቅም ግንባታ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ተፈራ ዋልዋ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ኩማ ደመቅሳ፤ በተጨማሪ ለአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን በየወቅቱ ለነበሩት ኃላፊዎች በነፃ ስልጠና እንድሰጥና ሞያዬን እንዳካፍል ይፈቀድልኝ ሲሉ በተደጋጋሚ ጠይቀዋል። ይህም ሆኖ አቶ ተገኑ በ71 ዓመታቸው ዳሸን ባንክ ከአርትስ ቴሌቪዥን ጋር ባካሄደው የስራ ፈጠራና የንግድ ውድድር ላይ ለመሳተፍ በቅተዋል። በዚህም ነሐሴ 26 ቀን 2012 ዓ.ም ውድድሩን ደረጃ በመያዝ አጠናቀው የሰርተፍኬትና የአምስት ሺ ብር ሽልማት ለማግኘት በቅተዋል።

በእኛ ዘመን የውሃ በቆሻሻ መበከልና ያለአግባብ መፍሰስ በስፋት ይስተዋል ስለነበር የአዳር ሰራተኞች ተመድበው በየሌሊቱ እየተሽከረከሩ ቁጥጥር እስከማድረግ የደረሰ እርምጃ ይወሰድ ነበር። ይህ ችግር በአሁኑ ወቅትም አለ። የሚሉት አቶ ተገኑ በዚህ ዘመን ደግሞ ነገሩን የባሰ የሚያደርገው አብዛኛው የውሃ መስመር ከውሃ መፍሰሻ ቦዮች ጋር አንድ ላይና የተቀራረበ መሆኑ የውሃ መስመሮችን ለመበከል ቅርብ ያደርጋቸዋል። በዛ ላይ ሁሉም የከተማዋ የውሃ መፍሰሻ ቦዮች በቆሻሻ ፍሳሽ የተሞሉ በመሆኑ የቧንቧ ውሃው የመበከል እድሉ ሰፊ ነው። አንዳንድ ጊዜ በየቤታችን የሚቀዳው የደፈረሰ ውሃም ለዚህ ምስክር ነው። በመሆኑም ችግሩ እንዲቀረፍ ዛሬም ብዙ መስራት ይጠበቃል ይላሉ።

## መልዕክት

እኔ በአሁኑ ወቅት ሰባ ስድስት ዓመት ሆኖኛል። በወጣትነቴ የአቅሜን ተሯሩጬ ስለሰራሁ የሚቸግረኝ ነገር የለም። በፈጣሪ እርዳታ ልጆቼም ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ በቅቺያለሁ። ነገር ግን እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ በየሰፈሩ ያለ ስራ ተቀምጠው የሚውሉ ወጣቶችን ስመለከት እረበሻለሁ። እነዚህን አልባሌ ቦታ እንዳይውሉና ለሱስ እንዳይዳረጉ የማድረጉ ኃላፊነት የመንግስት ብቻ ሳይሆን የእኛም ነው። እኔ እድሉን አግኝቼ ጥቂት በጣት የሚቆጠሩ ወጣቶችን አሰልጥኜ ስራ ቢይዙ የአእምሮ እረፍት አገኛለሁ። ወጣቶችም ሁኔታዎች ሙሉ ለሙሉ እስኪመቻቹላቸው ከመጠበቅ ተንቀሳቅሰው ለፍተው ራሳቸውን ሊያበቁ ይገባል እላለሁ።

በሌላ በኩል በአሁኑ ወቅት የአዲስ አባባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የሚሰሩትን እያየሁ ነው። በጣም የሚያስደስት ስራ ነው። በየመንገድ ዳርቻ የመፀዳጃ ቤት እየተገነባ ነው። ለዚህም አስር የእጅ መታጠቢያ የመጸዳጃ ቤት መቀመጫና ሌሎች አንዳንድ ነገሮችንም በስጦታ ለማበርከት ያዘጋጀሁ ሲሆን፤ ሁኔታዎች ሲመቻቹ የማበረክት ይሆናል። በእንዲህ አይነቱ ስራ መተባበር ከሌሎችም የሚጠበቅ ይሆናል ሲሉም አቶ ተገኑ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

# የቱሪስት ፍሰቱን ለማሳደግ ሌላኛው መሳ

**ዳግም ከበደ**

ቱሪዝም የበርካታ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎን የሚጠይቅ ዘርፍ ነው። በዓለማችን ካሉ ታላላቅ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የስራ እድል በመፍጠር ረገድም ወደር አይገኝለትም። ከአለም ሰራተኞች 10 በመቶ የሚሆኑት በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ ናቸው።

በዚህ መነሻ መንግስት፣ የግሉ ዘርፍና ግለሰቦች ለዘላቂ ቱሪዝም እድገትና አካታችነት ቅንጅታዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይጠበቃል። በአብዛኛዎቹ አገራት በጥቅል አገራዊ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው ድርሻም ከፍተኛ ነው። ያደጉ አገራት ሀብትና የሰው ኃይል አቅማቸውን በማቀናጀት ላቅ ያለ ጠቀሜታን ያገኙበታል።

ከቱሪዝም የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ለማላቅ ቅንጅታዊ አሰራር እንደሚያስፈልግ የዘርፉ ምሁራ በተደጋጋሚ ያስገነዝባሉ። ይህ መባሉም ሁሉም ባለድርሻዎች የተናበበና የተሰናሰለ ሕብረት መፍጠር እንደሚኖርባቸው ለማመላከት ነው።

ለዘላቂ ቱሪዝም እድገት መንግስት ፖሊሲ፣ ሕግና ስርዓትን ከማበጀት ጀምሮ የመስህብ ሀብቶችን በመጠበቅ፣ በማልማትና በማስተዋወቅ ከፍተኛ ድርሻን መውሰድ አለበት። የግሉ ዘርፍም እንዲሁ በሆቴልና በሌሎች መሰል አገልግሎቶች (hospitality and service)፣ በአስጎብኚ ድርጅት፣ በቱሪዝም ምርት አቅርቦቶች እና በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ላይ ንቁ ሆኖ መሳተፍ ይኖርበታል። ማህበረሰቡም የማንነቱ መገለጫ የሆኑ እሴቶቹን በመጠበቅና በማስተዋወቅ የድርሻውን መውሰድ እንዳለበት ይታመናል። ይህ ቅንጅት ሁለንተናዊ እድገት እንደሚያመጣ ይታሰባል።

በቱሪዝም ዘርፍ ውስጥ የማይተካ ሚና ከሚጫወቱት ውስጥ የሆስፒታሊቲ ዘርፉ በመጀመሪያዎቹ ረድፎች ላይ ይቀመጣል። ሆቴሎች፣ ሎጆች፣ ሪዞርቶች እና ሬስቶራንቶች ወደ አንድ አገር ለጉብኝት የሚገቡ ቱሪስቶች በቂ ማረፊያ፣ መዝናኛና የተሟላ አገልግሎት አግኝተው ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ በማድረግ በኩል ወሳኝ ድርሻ አላቸው።

በዚህ ሁሉ ምክንያት የኢትዮጵያ መንግስት ቱሪዝምን ከዋና ዋና ኢኮኖሚ ምሰሶዎች አንዱ አድርጎ ወስዶታል፤ ባለሀብቶችም መዋለ ንዋያቸውን በእዚህ ላይ እንዲያፈሱ እያበረታታ ይገኛል። በቱሪዝም ኢንቨስትመንት የግሉ ዘርፍ ከሚሳተፍባቸው ዋና ዋና መስኮች የሆስፒታሊቲ ዘርፉ ተጠቃሽ ነው።

የሆስፒታሊቲ ዘርፉ መነቃቃትና ወደ ላቀ ደረጃ መሸጋገር ቱሪዝም በዘላቂነት ውጤታማ እንዲሆንና ኢኮኖሚያዊ ጥቅምም እንዲገኝ እድል እንደሚከፍት ባለሙያዎች ያስረዳሉ። ቱሪስቶች ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ የተሟላና የአገር ገፅታን የሚገነባ መስተንግዶ አግኝተው ወደመጡበት እንዲመለሱ፤ በቀጣይም እምነት አግኝተው ዳግም ለጉብኝት እንዲመጡ የሆስፒታሊቲ መስኩ መዘመን የግድ እንደሆነ ባለሙያዎች ይመክራሉ። ጎብኚዎች በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ የመስህብ መዳረሻዎች እንዲመጡ የመሳብ አቅም ሊኖራቸው እንደሚገባ ያሳስባሉ።

አቶ ሳህሌ ተክሌ በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩት ጥናትና ምርምር ክፍል ከፍተኛ ተመራማሪ ነው። እርሱ እንደሚለው፤ ሆቴሎች፣ ሎጆችና ሪዞርቶች በራሳቸው ተነሳሽነት ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ የመስራት አቅም መፍጠር ይችላሉ። በአገሪቱ የሚገኙ ስማቸውን የገነቡ ባለኮኮብ ሆቴሎችን ጨምሮ በሆስፒታሊቲ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ዓለም አቀፍ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ለቱሪስት ፍሰቱ መጨመር ድርሻ ሊኖራቸው እንደሚገባም ያስረዳል።

በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ቱሪስቶች በብዛት የሚመጡት በአስጎብኚ ድርጅቶች እና በመዳረሻ ቦታዎች አማካኝነት እንደሆነ ጠቅሶ፣ ሆስፒታሊቲ ላይ የሚሰሩትም ለቱሪስት ፍሰቱ ማደግ የድርሻቸውን መወጣት እንዳለባቸው ይገለፃል።

> ‹‹መልካም ስም ተሻጋሪ ነው። ገበያ እንዲፈጠርና ቱሪስቱ ፍላጎት ኖሮት ቆይታ እንዲኖረው ያስችላል››

‹‹በአንድ የቱሪዝም መስህብ መዳረሻ ላይ በርካታ ሆቴሎች፣ ሎጆችና ሪዞርቶች ሊገኙ ይችላሉ›› የሚለው ከፍተኛ ተመራማሪው፤ ከዚህ ቀደም የነበረው ልምድ ቱሪስቶችን በስፍራው ሲገኙ ከማስተናገድና ማረፊያ ከማቅረብ የዘለለ ድርሻ እንደሌላቸው የሚያሳይ መሆኑን ያመለክታል። በኢትዮጵያ የቱሪስት ቁጥሩ እንዲጨምርና የአገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲያድግ ለማድረግ የሆስፒታሊቲ ዘርፉን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ስልት ነድፈው በቅንጅት መስራት እንደሚጠበቅባቸው ይገልፃል። ከዚህ መካከል የሆስፒታሊቲ ሚናን ማሳደግ አንዱ እንደሆነም ያስረዳል።

በሆስፒታሊቲ ዘርፉ ላይ የተሰማሩ ሆቴሎች በመዳረሻዎች አካባቢ ለሚገኙ ቱሪስቶች የሚሰጡት የተሟላና አርኪ አገልግሎት ቆይታቸውን ለማራዘም ምክንያት ይሆናል የሚለው ከፍተኛ የሆቴልና ቱሪዝም ተመራማሪው አቶ ሳህሌ፤ ከሌሎች የቱሪዝም ዘርፉ ባለድርሻዎች ጋር (አስጎብኚ ድርጅቶች፣ ሁነት አዘጋጆች፣ መዳረሻዎች) በመቀናጀት የኢትዮጵያን የቱሪዝም ዓለም አቀፍ ድርሻ ማሳደግ እንደሚችሉ ይገልፃል።

‹‹መልካም ስም ተሻጋሪ ነው። ገበያ እንዲፈጠርና ቱሪስቱ ፍላጎት ኖሮት ቆይታ እንዲኖረው ያስችላል›› የሚለው ከፍተኛ ተመራማሪው፤ ሆስፒታሊቲ ዘርፉ በቱሪዝም ላይ በጎ ተፅዕኖ እንዲኖረው የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን ማሳደግ እንደሚገባ ያስረዳል። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ከአንዳንድ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች ባሻገር ዓለም አቀፍ ቱሪስቱን በተሟላ ሁኔታ ሊያረካ የሚያስችል አገልግሎት ማግኘት አዳጋች መሆኑን አመልክቷል። ይህንን ለመቀየር የሚቀርበው ምርትም ይሁን አገልገሎት በቱሪስት ፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ጠቅሶ፤ ይህም የሆስፒታሊቲ ዘርፉን ስምና ዝና በሚመጥን መልኩ ሊቀናጅ እንደሚገባው ያመለክታል።

የቱሪዝም ዘርፉ እድገት እንዲፋጠን ሆስፒታሊቲ ዘርፉ ትልቅ ድርሻ እንዳለው የሚናገረው አቶ ሳህሌ፣ ከዚህ ውስጥ ሆቴሎች ዓለም አቀፍ የምርት ስም (Brand) መገንባት እንደሚጠበቅባቸው ጠቁሟል። ለዚህም የግዴታ ታዋቂ ከሆኑ ድንበር ተሻጋሪ የሆቴል ስሞች ጋር ትስስር መፍጠር እንደሚያስፈልግ በመግለፅ አዲስና አገራዊ የሆኑ ታዋቂ ስሞችን መገንባት እንደሚቻል ያስረዳል።

ለዚህም የኃይሌ ሪዞርትስ እና ሆቴሎች፣ የጁፒተርና ካፒታል ሆቴሎች አሁን የደረሱበትን እውቅና ደረጃ በምሳሌነት ይጠቅሳል። የኃይሌ ሆቴሎችን የመሳሰሉ ሌሎች በርካታ ታዋቂ የኢንዱስትሪው ተሳታፊዎችም ለቱሪዝም እድገትና ለቱሪስት ፍሰት መጨመር አዎንታዊ ድርሻ እንዳላቸው ይጠቁማል። የኢትዮጵያን መዳረሻዎች ሊጎበኝ የመጣ ቱሪስት እነዚህን አገልግሎት ሰጪዎች ተመራጭ ማድረጉ የማይቀር መሆኑን በማንሳት መሰል አርኪ አገልግሎት የሚሰጡ ስም ያላቸው ሪዞርቶች፣ ሎጆችና ባለኮኮብ ሆቴሎች ማስፋፋት እንደሚያስፈልግ ይናገራል።

‹‹ቱሪስቶች ከዋና ዋና መዳረሻዎች ጉብኝት ባሻገር ሁነቶች ላይ የመሳተፍ ፍላጎት አላቸው›› የሚለው አቶ ሳህሌ፤ ሆቴሎች፣ ሪዞርቶች፣ ሎጆችና የሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪው ተሳታፊዎች ከአስጎብኚ ደርጀቶች፣ ከሌሎች ባለድርሻዎች ጋር በመተባበር ቢሰሩ የተሻለ ውጤት ማምጣትእንደሚችሉ ይናገራል። የቱሪስት ቆይታን ከማራዘም አንፃርም መሰል ሁነቶችን ማሰናዳት ትልቅ ውጤት እንዳለው ነው ያመለከተው።

በሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪ ላይ የተሰማሩ (ሆቴል፣ ሪዞርቶች፣ ሬስቶራንት፣ ሎጆችና የባህል ቤቶች) የምግብ ቱሪዝም እንዲያድግ ደርሻቸው የላቀ ነው የሚለው ከፍተኛ ተመራማሪው፤ የኢትዮጵያን ባህላዊ ምግቦች ለመመገብ፣ ለማወቅ የሚመጡ ቱሪስቶችን ለመሳብ በእጅጉ ወሳኝ መሆናቸውን ነው የሚያስረዳው።

የባህል፣ የተፈጥሮ፣ የታሪክና ቀደም ያሉ የኪነ ሕንፃ ቅርሶችን እንዲሁም የአርኪዮሎጂካል ግኝቶቸን ለመጎብኘት ወደ ኢትዮጵያ በሚመጡበት ወቅት ባህላዊ ምግቦችን ለመመገብና ከአካባቢው ጋር ራሳቸውን ለማላመድ ፍላጎት እንደሚኖራቸው ጠቅሶ፣ ይህንን አገልግሎት በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል ቁመና በሆስፒታሊቲ ዘርፉ ላይ መኖር እንደሚገባው አቶ ሳህሌ ተክሌ ምክረ ሀሳቡን ሰጥቷል።

የዝግጅት ክፍላችን የቱሪስት ቆይታን ለማራዘምና ፍሰቱን ለመጨመር ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ከተመራማሪው ባሻገር ሆቴሎች የሚመለከታቸውን አካላትንም አነጋግሯል፡፡ ከእነዚህ መካከልም ሼባ ቪሌጅ ሪዞርትና እና ጃሎ ሆቴል ይገኙበታል።

ያብስራ አረጋዊ የሼባ ቪሌጅ ሪዞርት ፍሮንት አፊስ ባለሙያ ነው። የኦሮሚያ ቱሪዝም ሳምንት በስካይ ላይት ለሶስት ቀናት ሲዘጋጅ የሼባ ቪሌጅን የምርት ስም (Brand) ሲያስተዋውቅ ነበር። እርሱ እንደሚለው፤ በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኘው ሪዞርታቸው በርካታ የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች ማረፊያ ነው። በ25 ሺህ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈው ይህ ሪዞርት ጎብኚዎች ወደ ከተማዋ በሚመጡበት ወቅት ቆይታቸውን አራዝመው፤ ተዝናንተውና ከተማዋን ጎብኝተው እንዲሄዱ ምቹ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በዚህም ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ተጨማሪ አቅም እየሆነ ነው።

‹‹ቢሾፍቱ በሀይቅ ዳርቻዎቿ በስፋት ትታወቃለች። ሼባ ቪሌጅ ሪዞርት ግን ሌላኛውን የከተማዋን ገፅታ የሚያሳይ ነው›› የሚለው የፍሮንት አፊስ ባለሙያው፤ ሪዞርቱ በተራሮች የተከበበና ለጎብኚዎች ማራኪ እይታን በሚፈጥር አቀማመጥ ላይ እንደሚገኝ ያስረዳል።

እንደ ባለሙያው ገለፃ ፤ የሼባ ቪሌጅ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች በከተማዋ ምቹ ቆይታን እንዲያደርጉ ታስቦ የተገነባ ነው። 20 ቪላ ቤቶች በባለ ሶስት እና በባለ አምስት መኝታ ቤቶች ሲኖሩት እያንዳንዳቸው 500 ካሬ ሜትር ላይ ያረፉ መሆናቸውን ያስረዳል። ይህም ቱሪስቶች የሚፈልጉትን ምቾትና የግል ደህንነት እንዲያገኙ የሚያስችል ነው። በተጨማሪ ተፈጥሮን ለመመልከትና ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ የተራራ መውጫ (hiking) እና ሌሎች ተዝናኖት የሚፈጥሩ ሁነቶች እንደሚያዘጋጅ ነግሮናል። በቀጣይ ሪዞርቱ ለቱሪዝም ዘርፍ ተጨማሪ አቅም መፍጠርና ኢትዮጵያ ተመራጭ መዳረሻ እንድትሆን የመስራት እቅድ መያዙንም አስረድቶናል።

ሌላኛው የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገረው በሻሸመኔ ከተማ የሚገኘውን የጃሎ ሆቴል የሩም ዲቪዥን ማኔጀር የሆነውን ዳግም ጌቱን ነው። እርሱእንደሚለው የሆስፒታሊቲ ዘርፉ ለቱሪዝም እድገት ከፍተኛ ደርሻን ይወስዳል። ኢንዱስትሪው ያለ ሆስፒታሊቲ ዘርፉ አንካሳ መሆኑንም ይገልፃል። እርሱ በሩም ዲቪዥን ማኔጀርነት የሚሰራበት ጃሎ ሆቴልም ቱሪዝም በኢትዮጵያ የተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አስተዋፆ ለማድረግ በማሰብ የተቋቋመ ነው።

ጃሎ ሆቴል በሻሸመኔ ከተማ የሚገኝ ባለ አራት ኮኮብ ሆቴል መሆኑን የሚገልፀው ሩም ዲቪዥን ማኔጀሩ፤ ለሶስት ዓመታትም የውጪ እና የአገር ውስጥ ቱሪስቶችን በእንግድነት በመቀበል የተሟላ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱን ይናገራል። ከተማዋ አምስት መግቢያ በሮች እንዳሏት በመግለፅም ቱሪስቶች፣ ኤግዚቢሽን፣ ስብሰባ እንዲሁም ሌሎች ሁነቶች ላይ የሚሳተፉ ተጓዦች ምርጫቸው ስለሚያደርጓት በቂ የሆስፒታሊቲ አቅርቦት መስጠት እንደሚያስፈለግ ያነሳል። ጃሎ ሆቴልም ይህንን ክፍተት ለመሙላት መቋቋሙን አስታውቋል።

‹‹በቱሪስቶች ከፍተኛ ተመራጭ እና በኢትዮጵያ ሁለተኛው የሆነውን የደቡብ ኢትዮጵያ የቱሪዝም መስመር ተደራሽ ለመሆን እየሰራን ነው›› የሚለው ማኔጀሩ ዳግም ጌቱ፤ ወደ ባሌ፣ ወደ አርባ ምንጭ፣ ወደ ሀዋሳ፣ የሚደረገው ጉዞ እንዲያቀላጥፍና የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር እየተጉ እንደሆነ ያስረዳል።

በየዓመቱ በሚካሄደው የኦሮሚያ ቱሪዝም ሳምንት ጃሎ ሆቴል ባሳለፍነው ዓመት በምርጥ የቱሪስትና የደንበኞች አገልግሎት ዘርፍ የዋንጫ ተሸላሚ ነበር። ምርጫው ላይ ድምፅ የሰጡት ደንበኞች እና ቱሪስቶች ናቸው። ሆቴሉ ለቱሪስቶች የተራራ መውጣትና የእግር ጉዞ ከማዘጋጀት ባሻገር ለጉብኝት ተመራጭ የሆኑ መዳረሻዎችን በመጠቆም ተወዳጅ መሆኑንም ዳግም ነግሮናል። ይህን መሰል አገልግሎት በሁሉም በሆስፒታሊቲ ዘርፉ ላይ በሚገኙ የኢንዱስትሪው አንቀሳቃሾች ተግባራዊ ቢሆን አሁን ካለው የቱሪስቶች ቁጥር በበለጠ ኢትዮጵያ ማስተናገድ እንደምትችል አስታውቋል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በኢትዮጵያ በርካታ የመስህብ ስፍራዎችና መዳረሻዎች ቢኖሩም ይህንን የሚመጥን የቱሪስት ፍሰት ግን የለም። በየዓመቱ አንድ ሚሊዮንና ከዚያ በታች የሆነ ዓለም አቀፍ ጎብኚ ብቻ ኢትዮጵያን እየጎበኘ ነው።

በተቃራኒው ከኢትዮጵያ ያነሱ መስህቦች ያላቸው አገራት በሆስፒታሊቲ፣ በማስተዋወቅና በሌሎች የአገልግሎት ዘርፍ ጥራት ያለው አቅርቦት ስላላቸው ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጎብኚ ያስተናግዳሉ። በዚህ ምክንያት በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ትኩረታቸውን አድርገው የሚሰሩ ባለሙያዎች ኢትዮጵያ ስኬታማ የቱሪዝም ዘርፍ ለመገንባት እና ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመፍጠር የመንግስትንና የግሉ ዘርፍ አቅም አቀናጅታ መስራት እንደሚጠበቅባት ይመክራሉ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የሰገሌ ጦርነት በዛሬዋ ቀን

ዋስልኝ አየለ

በኢትዮጵያ ውስጥ ከተደረጉ የጦርነት ታሪኮች ውስጥ የሰገሌ ጦርነት አንዱ ነው። በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ከ108 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት በዛሬዋ ቀን ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም የተደረገውን የሰገሌ ጦርነት ዘርዘር አድርገን እናስታውሳለን።

በሌላ በኩል ከ116 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 15 ቀን 1900 የተመሰረተውን የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ የመከላከያ ሚኒስቴር (በያኔው አጠራር የጦር ሚኒስቴር) እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው በዚህ ሳምንት የተከናወኑ ሌሎች ዓለም አቀፍ እና የአገር ውስጥ ታሪኮችን እናስታውስ።

ከ92 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 13 ቀን 1925 ዓ.ም ታላቁ ሠዓሊ እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ተወለዱ።

ከ79 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 14 ቀን 1938 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (United Nations) በይፋ ተመስርቶ ስራ ጀመረ (ቻርተሩ በስራ ላይ መዋል መጀመሩ ተበሰረ)። ከቅኝ ገዢ ኃይሎች ነፃ የነበረችው ኢትዮጵያም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መስራች ነበረችና በወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው የተመራው የልዑካን ቡድን ሰኔ 19 ቀን 1937 ዓ.ም ሳን ፍራንሲስኮ ከተማ ላይ፣ በሳን ፍራንሲስኮ የጦር መታሰቢያና ኪነ ጥበብ ማዕከል ውስጥ የድርጅቱን የቃል ኪዳን ሰነድ (የመመስረቻ ስምምነት/Charter) ፈረመ።

ከ51 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 15 ቀን 1966 ዓ.ም ሻምበል አበበ ቢቂላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

ከ117 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 15 ቀን 1900 ዓ.ም ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የመከላከያ ሚኒስቴር (የጦር ሚኒስቴር) መሥሪያ ቤትን አቋቋመች። ይህን መነሻ በማድረግ በየዓመቱ ጥቅምት 15 ቀን «የሠራዊቱ ቀን» ሆኖ እንዲከበር ተወስኗል። ባለፈው ዓመት የመከላከያ ቀን «ለ116ኛ ጊዜ» ተብሎ እንደተከበረ እናስታውሳለን። የዘንድሮው በዜና ሽፋን ስለሚዘረዘር (ይህ ጽሑፍ ከጥቅምት 15 በፊት የተዘጋጀ ነው) ከ117 ዓመታት በፊት የነበረውን ሁነት እናስታውስ።

የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንደሚሉት፤ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» የሚል አመለካከት አልነበራቸውም። ለመንግሥት ድርጅታዊ መሰረትና ቀጣይነት ለመስጠት በ1900 ዓ.ም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን አቋቋሙ። እንደ ፕሮፌሰሩ ገለጻ፤ የመጀመሪያዎቹ ሚኒስትሮች አዲስ አውሮፓዊ ካባ የለበሱ የቤተ መንግሥት ባለሟሎች ናቸው። ይህም የዳግማዊ አጼ ምኒልክን ባህል እና ዘመናዊ ሥልጣኔን የማስታረቅ ፍላጎት ነው።


የጦር ሚኒስቴር ዋና ተግባር የነበረው የጦር ሥልጠና መስጠት ሲሆን፤ የመጀመሪያው የጦር ሚኒስትር ፊት አውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ መሆናቸው ይታወሳል።

ከ113 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 17 ቀን 1904 ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በአርበኝነት ተጋድሎ ዘመን የማይሽረው አኩሪ ገድል ከፈፀሙት ኢትዮጵያውያን አርበኞች መካከል አንዷ የሆኑት ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ከበደች ስዩም ተወለዱ።

አሁን በዝርዝር የምናየውን የሰገሌ ጦርነት እናስታውስ። ከ108 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም፤ መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ ሚካኤል በሸዋ መኳንንትና ኢትዮጵያን ለመቀራመት አሰፍስፈው ይጠብቁ በነበሩ የውጭ ኃይሎች ሴራ ከአልጋ ወራሽነታቸው ከተሻሩ በኋላ፣ አባታቸው ንጉሥ ሚካኤል አሊ የልጃቸውን ስልጣን ለማስመለስ ባደረጉት ጥረት፣ ከማዕከላዊ መንግሥቱ ጦር ጋር የመጨረሻውን ጦርነት፣ ሰገሌ ላይ፣ አደረጉ።

የሰገሌ ጦርነት በሥልጣን ሽኩቻ ከተደረጉ የእርስበርስ ጦርነቶች ሁሉ በአስከፊነቱ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው። ከዛሬ 108 ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ምን ያህል ይሆን ነበር? የሚለውን ታሳቢ እናድርግና 16 ሺህ ያህል ሰዎች የተጨፋጨፉበት ጦርነት ነው።

የሰገሌ ጦርነት መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ ሚካኤል በመኳንንትና ኢትዮጵያን ለመቀራመት አሰፍስፈው ይጠብቁ በነበሩ ቁሳራውያን (እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ እና ጣሊያን) ኃይሎች ሴራ ከአልጋ ወራሽነታቸው



የሰገሌ ጦርነት መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ነበር የተደረገው፣

ከተሻሩ በኋላ፣ አባታቸው ንጉሥ ሚካኤል አሊ የልጃቸውን ስልጣን ለማስመለስ ከማዕከላዊ መንግሥቱ ጦር ጋር የመጨረሻውን ጦርነት ያደረጉበት ነው።

በ1906 ዓ.ም በልጃቸው አማካኝነት «የወሎ፣ የትግሬና የጎጃም ንጉሥ» ተብለው የተሾሙት ንጉሥ ሚካኤል አሊ፣ በ1909 ዓ.ም የልጃቸውን ከዙፋን መሻር ሲሰሙ «ቢያጠፋ እንኳ እኔ እመክርና አርመው የነበረውን ልጄን እንዴት ሳያማክሩኝ የአባቱን ዙፋን ያስለቅቁታል?» በማለት «የጠፋ ልጄን አፋልጉኝ» ብለው 80 ሺህ ወታደሮቻቸውን አስከትለው ወደ ሸዋ ዘመቱ።

የንጉሥ ሚካኤልን ጦር ለመግጠም በማዕከላዊው መንግሥት በኩል 120 ሺህ ጦር ተዘጋጅቶ የመጀመሪያው ጦርነት ከዋናው ጦርነት ቀደም ብሎ ጥቅምት 7 ቀን 1909 ዓ.ም በደብረ ብርሃንና አንኮበር መካከል በሚገኘው ቶራ መስክ ላይ ተካሄደ።

በቶራ መስክ ጦርነትም የንጉሥ ሚካኤል ጦር አሸነፈ። በዚህ ውጊያ ላይ የሸዋው የጦር መሪ ራስ ልዑልሰገድ አጥናፍሰገድን ጨምሮ በርካታ የጦር አዛዦችና ወታደሮች አለቁ። ለጦርነቱ 120 ሺህ ጦር ይዘጋጅ እንጂ ከዚህ መካከል ቁጥሩ በርከት ያለው የሸዋ ጦር ከንጉሥ ሚካኤል ጦር ጋር የተዋጋው ሰገሌ ላይ ነበር።

ከድሉ በኋላም፤ የጦር ሚኒስትሩና የማዕከላዊው መንግሥት ቁልፍ ሰው የነበሩት ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ (አባ መላ) ገፀ በረከትና ላይ ላዩን ሲያዩት እርቅ ውስጥ ውስጡን ደግሞ ማዘናጊያ የመሰለ ቃላት በመላክ የወሎው ጌታና ጦራቸው ተዘናግተው እንዲቆዩ አደረጉ። «በሰላም መወያየቱ ይሻላል» የሚል ሃሳብ ያለውና ውሉ ያልለየውን ቃል የሰሙት ንጉሥ ሚካኤልም የመጀመሪያው ድላቸውን እንደጨበጡ ሰገሌ ሜዳ ላይ ሰፍረው ቆዩ።

ከቶራ መስኩ ጦርነት 10 ቀናት በኋላ ዋናውን ጦርነት ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም የንጉሥ ሚካኤል ጦርና የማዕከላዊው መንግሥት ጦር ሰገሌ በተባለው ሜዳማ ስፍራ ላይ ከባድ ጦርነት አካሄዱ። የማዕከላዊው መንግሥት ቁልፍ ሰው በነበሩት በጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ እቅድ አውጪነትና መሪነት ለቀናት ያህል በስውር ከበባ ሲያደርግ የቆየው የማዕከላዊው መንግሥት ጦር የወሎን ጦር ባላሰበው መንገድ አጠቃው።

በዚህ ጦርነት ላይ የጦር ሰራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ ሆነው የዘመቱት ራስ ተፈሪ መኮንን ሲሆኑ ከእርሳቸው ጋርም ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ እና ራስ ካሳ ኃይሉ መሪ ሆነው ተሳትፈዋል። በውጊያውም የንጉሥ ሚካኤል ጦር ያለቀው አልቆ የተረፈው ሲበታተን ንጉሥ ሚካኤልም ተማረኩ። የሰገሌው ጦርነት ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ብዙ ሰው ያለቀበት ከባዱ ውጊያ እንደነበር በታሪክ ተመዝግቧል።

ንጉሥ ሚካኤል በሰገሌው ጦርነት ተሸንፈው፣ ተማርከው አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ሲያልፉ ክብራቸው ተዋርዶ እንደነበር የታሪክ ጸሐፍት አስፍረውታል።

«ሐበሻና የሰገሌው አብዮት» የሚለውን መፅሐፍ የፃፈው እንግሊዛዊ ጸሐፊ በበኩሉ« ...ንጉሥ ሚካኤል ሀገሪቱ አሉኝ ከምትላቸው ጀግና የግዛት አስተዳዳሪዎችና የጦር መሪዎች አንዱ ነበሩ ... ያ ከንቱ ልጅ ከከብራቸው ዝቅ እንዲሉ አደረጋቸው...» በማለት ጽፏል።

በእርግጥ የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ እንግሊዛዊ በመሆኑና እንግሊዝ ከማዕከላዊው መንግሥት ሹማምንት ጋር በማሴር ልጅ ኢያሱ ከዙፋናቸው እንዲሻሩ ትልቁን ድርሻ የተወጣች ቁሳራዊ ኃይል ስለሆነች ፀሐፊው እንደዚያ ብለው ቢጽፉ የሚገርም አይደለም፤ በመጽሐፉ ውስጥ በርካታ የተዛቡ ታሪኮች አሉ የሚል ወቀሳም ሲቀርብበት ነበር።

«ተፈሪ መኮንን፡ ረጅሙ የስልጣን ጉዞ» በሚለው የክቡር አምባሳደር ዘውዴ ረታ መጽሐፍ ላይም ስለ ጦርነቱና ከውጊያው በኋላ ስለተፈፀሙት ድርጊቶች ተብራርቷል።

በሰገሌው ጦርነት ላይ የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት እንዳለ የተለያዩ የታሪክ ጸሐፊዎች ጽፈዋል። ልጅ ኢያሱ መፈንቅለ መንግሥት እንዲደረግባቸው አድርገዋል። በነገራችን ላይ እርሳቸው በቀጥታ «መፈንቅለ መንግሥት» ባይሉትም ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ «ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ» በሚለው መጽሐፋቸው መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም በልጅ ኢያሱ ላይ የተደረገውን አድማ በገደምዳሜው ገልጸውታል። ካህናቱና መኳንንቱ ከዚህ በኋላ ልጅ ኢያሱን አውርደን የአጼ ምኒልክን ልጅ ዘውዲቱን አንግሰናል ማለታቸውን ራሳቸው አጼ ኃይለሥላሴ ጽፈዋል።

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ከአድዋ ድል በኋላ የቆዩባቸው አስር ዓመታት (ከ1888 ዓ.ም እስከ 1898 ዓ.ም) የሰላምና የመረጋጋት ወቅት እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። ንጉሡ ታመው አልጋ ላይ ሳሉ የሥልጣን ሽኩቻ እንዳያገረሽ በማሰብ መላ ዘየዱ። በወቅቱ በጎረቤት አገራት የቅኝ ግዛት ይዘው የነበሩት እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን በለንደን የሦስትዮሽ ውል ተፈራርመው «እርስዎ ድንገት ቢያርፉ አገር እንዳትበጠበጥ ሦስታችን መንግሥታት የበላይ ጠባቂ ሆነን አገር ለማረጋጋት...» የሚል ይዘት ያለው ደብዳቤ ለምኒልክ ይልካሉ። ንጉሡም አገሪቱን ለጅቦች አሳልፎ ላለመስጠት ለሦስቱ አገራት ቅኝ ገዥዎች በማያሻማ መልክ ግልፅ ያለ መልዕክት አስተላለፉ። « እኔ ብሞት ኢትዮጵያ በአልጋ ወራሼ አማካይነት ትቀጥላለች፤ የተረጋጋ ሥርዓትም እናቆማለንና አታስቡ » ካሉ በኋላ እርምጃዎችን ወሰዱ።

በወቅቱ ንጉሥ ምኒልክ ሲሞቱ በይፋ ያልተገለጸበት ምክንያትም የአገር ውስጥ የሥልጣን ሽኩቻ ይቀሰቀሳል፤ በጎረቤት አገሮች ያሉ ያደፈጡት ቅኝ ገዥዎችም አደጋ እንዳይደቅኑ በመስጋት ሊሆን እንደሚችል ሰነዶች ያስረዳሉ።

በወቅቱ በ1900 ዓ.ም በሀገሪቱ የመጀመሪያውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት አቋቋሙ። ከወሎው ኢማም መሀመድ አሊ (ራስ ሚካኤል) የተወለደው የልጅ ልጃቸው ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሻቸው መሆኑን አወጁ።

ልጅ ኢያሱ ገና ልጅ ስለነበሩም የሸዋው ራስ ተሰማ ናደውን የልጅ ኢያሱ ሞግዚት አድርገው ሰየሙ። ራስ ተሰማ ሲሞቱ ሌላ ሞግዚት ለመሰየም እየተከናወነ ባለው ተግባር በመኳንንቱ ዘንድ እኔ እሆን እኔ እሆን የሚል ነገር ተከሰተ፤ ሁኔታው ያላማራቸው ልጅ ኢያሱ በሸዋ ሞግዚት አያስፈልገኝም ወደሚል ድምዳሜ ደረሱ። ይህ የሚሆነው አጼ ምኒልክ ታመው በነበሩበት ወቅት ነው።

ልጅ ኢያሱ በአስተዳደር ቆይታቸው በጠረፍ አካባቢዎች የሚያደርጉት ተደጋጋሚ ጉብኝት በመኳንንቱ ዘንድ አልተወደደም።

በአገር ውስጥ ከሃይማኖት ጋር ጭምር የተያያዘ ሽኩቻ ሲነዛ በውጭ ደግሞ፤ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ከእንግሊዝ ፈረንሳይና ጣሊያን በተፃራሪ ደረጃ ለነበሩት ጀርመንና ቱርክ ድጋፋቸውን አሳይተዋል በሚልም በሌሎቹ ነጮች ዘንድ ጥርስ ተነከሰባቸው፤ በአገር ውስጥም አድማ ተጠነሰሰባቸው።

በእነዚህ ምክንያቶች በልጅ ኢያሱ መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ከሥልጣን ተሽረው (መፈንቅለ መንግሥት) ዘውዲቱ ምኒልክ ንግሥት እና ተፈሪ መኮንን ደግሞ አልጋ ወራሽ መሆናቸው ይፋ ተደረገ።

ይህኔ ነው የልጅ ኢያሱ አባት ጦራቸውን አዝምተው ከማዕከላዊው መንግሥት ጋር በተደረገ ጦርነት ያ ሁሉ ደም አፋሳሽ እልቂት የተከሰተው።

እንግዲህ ከዚህ ምን እንማራለን ከተባለ፤ የውጭ ሴራ ከድሮም ጀምሮ የነበረ መሆኑን እና የውስጥ የሥልጣን ሽኩቻ ድሮም የነበረ መሆኑ ነው። የሥልጣን ፍላጎት እንጂ የዘር አለመሆኑን ነው። ምክንያቱም የተላለቀው የአንድ አካባቢ ሕዝብ ነው። ልጅ ኢያሱ የአጼ ምኒልክ የልጅ ልጅ ነው። ዘውዲቱ የአጼ ምኒልክ ልጅ ናት። ስለዚህ ኢያሱን ገልብጦ ዘውዲቱን ማንገስ ከሥልጣን ፍላጎት ውጭ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

ከመቶ ምናምን ዓመታት በፊት የነበሩ የታሪክ ክስተቶችን የምናስታውሰው ዛሬ ዓለም የሥልጣኔ ማማ ላይ ባለበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ሆነን ነው። ስለዚህ ዘመኑን የሚመጥን አስተሳሰብ ይኑረን እና ታሪክን እንዲህ በታሪክነቱ ብቻ የምናስታውሰው እንሁን!

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

# የቲያትር ንግስቷ - ባዩሽ

ቤዛ እሸቱ

ለኪነ ጥበብ በልክ የተሰፋች ናት ይሏታል። ደራሲም ናት። ምንም እንኳን የግጥም መድብሏ የታተመው እሷ ካረፈች በኋላ ቢሆንም ግሩም የግጥም አዘጋጅ እንደነበረችም ይነገርላታል። ደግሞም በመረዋ ድምጿ በርካታ መጽሀፍትን በትረካ ሕይወት ዘርታባቸዋለች። የቅርብ ወዳጆቿና ጓደኞቿ በቁልምጫ ባዩ ይሏታል። ቲያትረኛ፣ ገጣሚ፣ ተዋናይ፣ አዘጋጅና ተራኪ አርቲስት ባዩሽ አለማየሁ።

አርቲስት ባዩሽ አለማየሁ ጥበብን የተቀበለችው ከአባቷ ይመስላል። ወላጅ አባቷ እውቁ የትርጉም ባለሙያ መስፍን አለማየሁ ነው። ተርጓሚ፣ ደራሲና ጋያሲም ነው። በተለይ የሼክስፒርን ድርሰቶችና የሩሲያ ድርሰቶችን በግሩም ሁኔታ በመተርጎም ይታወቃል። ካፖርቱና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች፣ የመጨረሻዋ ቅጠልና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች፣ ባህሩና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች በመጽሀፍ ካሳተማቸው ሥራዎች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

የአባቷ አባት አቶ አለማየሁ ጠይቃቸው ቤታቸው በልጆች ድምቀት ቢሞላም የአይን ማረፊያ የምትሆን ሴት ልጅ በማጣታቸው ሁሌ ሴት ልጅ ይመኙ ነበር። ግራ ቢገባቸው በየቤተክርስቲያኑ ሌሎች በሥለት ልጅ ተሰጠን ሲሉ ቢሰሙ ባለቤታቸውን እስቲ ሴት ልጅ እንዲሰጠን ተሳይ እስከ ማለት የደረሰ የሴት ልጅ ፍቅር ነበረባቸው። ይህን የባለቤታቸውን የሴት ልጅ ፍቅር የሚያውቁት ሴት አያቷ ወይዘሮ ፈሰስወርቅ ኃይሌ ባለቤታቸው ካረፉ በኋላ የተገኘች የልጅ ልጃቸውን "ምነው አለማየሁ ቢያይሽ ኖሮ" ሲሉ ባዩሽ አለማየሁ የሚል ሥም አወጡላት።

በ1969 በአዲስ አበባ ፒያሳ የተወለደችው ባዩሽ፤ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በመድኃኒአለም አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትላለች። ቤተሰቦቿ መክሊቷን ለመረዳት ጊዜ እንዳልፈጀባት እማኞች ናቸው። ከልጅነቷ ጀምሮ ታነባለች፤ እጇን ከወረቀት አገናኝታ ለመጻፍ እድሚዋ ከፍ እስኪል አልጠበቀችም። ትያትር ቤት ከመቀጠሯ አስቀድሞም በአማተርነቷ በርካታ የጥበብ ሥራዎችን ሠርታለች። "ሰቀቀን"፣ "የፍቅር ዜማ"፣ "እቡይ ደቀመዝሙር"፣ "የከፉ ቀን ደራሽ"፣ "የሁለት ቤት ድግስ"፣"የፌዝ ዶክተር"፣ "ማን ይንገራት?" የተሰኙ ትያትሮችን ከእውቅ ተዋናዮች ጋር የመተወን አጋጣሚን ያገኘቻው ገና በለጋ እድሜዋ ነበር።

በአማተርነቷ ዘመን ከትያትር ትወናዋ ባሻገር የሬድዮ ድራማዎችንም ትሰራ ነበር። በመላኩ አሻግሬ ከሚመራው ቴዎድሮስ የትያትር ቡድን ጋር "አንድ ጡት" እና "ማሪኝ" የተሰኙ ተውኔቶችን በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል በመዘዋወር አሳይታለች።

1990 ዓ.ም "አድጌበታለሁ የደስታ ጊዜያቶችን እንዲሁም ሐዘኔን አልፌበታለሁ" የምትለውና ረዥም ጊዜ የሠራችበትን የሀገር ፍቅር ትያትር ቤት የተቀላቀለችበት ዓመት ነበር። በሀገር ፍቅር ቆይታዋም "የጣር ሳቅ"፣ "ጥንድ መንገደኞች"፣ "ጣውንቶቹ"፣ "የቀትር ጥላ"፣ "ሰማያዊ አይን"፣ "ረመጥ"፣ "ትዳር ሲታጠን"፣ "የብዕር ሥም"፣ "የጉድ ቀን"፣ "አሉ" እና ሌሎችም ትያትሮች ላይ በመሪ ተዋናይነት ተውናለች። ትያትር በመጻፍ ለትያትር በልኩ የተሰፋች መሆኗን አስመስክራለች።

በአንድ ወቅት "ሰማያዊ አይን"ና "ረመጥ" የተሰኙ ሁለት ትያትሮችን የዋና ገጸባህሪን ተላብሳ ያለምንም እረፍት በተከታታይ ተጫውታለች። የሼክስፒር ድርሰት የሆነውንና በአባቷ የተተረጎመው "የቬኑሱ ነጋዴ" ትያትር ላይ የሴትንም የወንድንም ገጸ-ባህሪ ተላብሳ ተውናለች። በትያትሩ ላይ መጀመሪያ ከምትጫወታት የሴት ገጸ-ባህሪ ወደ ወንድ ጠበቃነት ስትቀየር በአለባበስና በገጽ ቅብ ብቻ ሳይሆን ከድምጿ አንስቶ በሁለንተናዋ ታዳሚ ወንድ መሆኗን አሳምና አስደምማለች።

የሙያ ባልደረቦቿ ባዩሽ ከራሷ በላይ ለኪነጥበብ ከበቂ በላይ የተገዛች መሆኗን ይመሰክራሉ። ለዚህ በርካታ ማሳያዎች ቢኖሩም አንዱ ማሳያ የተከሰተው ሀገር ፍቅርን ተቀላቅላ ብዙም ሳትቆይ ነበር። የኪነጥበብ ሰው በዓልን ከሕዝብ ጋር ማሳለፍ እንግዳው አይደለምና እሷም በፋሲካ ዋዜማ ምሳዋን በልታ በወቅቱ ትተውንበት የነበረው "የጣር ሳቅ" ትያትር ላይ ለመተወን ጉዞ ወደ ትያትር ቤቱ። የትያትር ቤቱ በር ከርቀት ይታያል፤ በርካታ ሰዎች ከትያትር ቤቱ አቅጣጫ ወደእሷ በሩጫ ሲመጡ ብታይም መንገድ ላይ የሚሸጡትን ሰዎች ደንብ አስከባሪዎች እያባረሯቸው ነው ብላ ስላሰበች ሰዉ ወደሚሸሽበት አቅጣጫ ጉዞዋን ቀጠለች። በዚህ መሃል ፊት ለፊት ሰው ሁሉ ፈርቶ ሲሸሸው ከነበረው የደነበረ በሬ ጋር ስትፋጠጥና በሬው በቀንዱ ወደ መሬት ሲቀላቅላት እኩል ሆነ።

መጎዳቷን ያዩና በተዋናይነቷ የሚያውቋት ሰዎች አንስተው ወደ ትያትር ቤት ወሰዷት። የወቅቱ የትያትር ቤቱ ሥራ አስኪያጅ "ወደሆስፒታል ሄደሽ ታከሚ ትያትሩን ሊያይ የመጣን ታዳሚ ይቅርታ ጠይቀን ለሳምንት እንቀጥራለን" የሚል ሀሳብ ቢያመጣም ባዩሽ ግን ልትስማማ አልቻለችም። ይልቁንስ ከህክምና መልስ ትያትሩን እንደምትሰራ ተናገረች። ይቅርብሽ ብትባልም ሞያውን አክብሮ ቀኑን ሰውቶ ረዥም ሰልፍ ይዞ የጠበቀን የትያትር ተመልካች አክብራ ከህመሟ ጋር ታግላ ለመስራት ወሰነች። ራስ ደስታ ሆስፒታል ተወስዳ ቁስሏ ታሽጎ ቁስሏን በሻሽ ሸፍና ተወነች።

አብረዋት የሠሩ ተዋናዮችና አዘጋጆች ገና የትያትር ልምምድ ሲጀመር ከሌሎቹ ቀድማ ገጸ-ባህሪዋን በመረዳት ይጠቅሷታል። እራሷ ከምትደርሳቸው ተውኔቶች ባሻገር የሌሎች ድርሰቶችንም ያልመሰላት ነገር ሲገጥማት እንዲህ ቢሆንስ በሚል ደራሲውን በማስፈቀድ ድርሰትን በማቃናት ትታወቃለች። አርቲስት ኪሮስ ኃይለሥላሴ የተውኔት ዝግጅት ላይ ቃለተውኔትን በማረም ጎበዝ እንደነበረች ያስታውሳል። ታዲያ ያኔ በማናለብኝነት እና እኔ አውቃለሁ ተሳስታችኋል ሳይሆን "ይህ እንዲህ ቢሆንስ" ማለት የሷ መለያ ነው። ለተወሰነ ጊዜ ከሀገር በመውጣቷና ወደ ጀርመን በማምራቷ ከትያትር አፍቃሪያን እሷም ከምትወደው መድረክ ተራርቃ ቆይታ ነበር። ሆኖም ከሀገሯም ከምትወደው የትያትር መድረክም ተለይታ መቆየት አልቻለችምና ወደ ሀገሯ ተመለሰች።ወደ ሀገሯ ተመልሳ ሰማያዊ ዓይን፣ ሰዓት እላፊ፣ ነቃሽ፣ አሉ በተሰኙ ትያትሮች በመተወን ወደ መድረክ ተመልሳለች።

ከጀርመን መልስ እሷ የተወነችባቸው ሰማያዊ አይን፣ ነቃሽና ሰዓት እላፊን ያዘጋጀው ተፈራ ወርቁ በዚህ የዝግጅት ጊዜ ባዩሽ ምን ያህል አዘጋጅን የምታግዝ መሆኗን ማየቱን ጠቅሷል። የማይመስላት ነገር ሲኖር ሰው ፊት የማትናገር የሞያ ሥነ-ምግባር ያላት መሆኗን ከፋና ቲቪ ጋር በነበረው ቆይታ ምስክርነቱን ሰጥቷል። ባዩሽ ዋነኛ መታወቂያዋ የመድረክ ትያትር ቢሆንም በቴሌቭዥንና በሬድዮ ድራማም፣ በፊልምም ሆነ በማስታወቂያዎች በመተወን ብቃቷን አሳይታለች። "ንስር"፣ "ፍለጋ"፣ "ስደት" የተሰኙት ፊልሞች ላይ ብቃቷን ያስመሰከረች ሲሆን፤ በተከታታይ የቴሌቭዥን ድራማ "አልተገናኘቶም"፣ "የማለዳ ጤዛ"፣ "አሳንሰር"፣ "አቋራጩ"፣ "አስታራቂ"፣ "ሻሞ"፣ "ሔዋን"፣ "እጣ"፣ "አዲስ ድባብ" ተጠቃሽ ናቸው። በሬድዮ ድራማ "መንታ መንገድ"፣ "የተከፋፈሉ ልቦች"፣ "የተዳፈነ ልብ"፣ "ጽናት"፣ "መስዋዕት"፣ "የሙት ልጅ"፣ "ወፌ ቆመች" ባዩሽ በድንቅ ብቃት የተወነችባቸው የሬድዮ ድራማ ርዕሶች ናቸው።

ባዩሽ ከመድረክ ጀርባ ስትታይ አጠር ብላ መድረክ የምትሞላ አትመስልም። ይህ ግምት ግን መድረኩ ላይ ስትወጣ እውነታው ሌላ ሆኖ ቁጭ ይላል። እሷ መድረክ ላይ ስትወጣ አጭር ቁመቷ ረዝሞ ቀጠን ያለው አካሏ ወፍሮ መድረኩን ትሞላዋለች። የሚያውቋት ከራሷ በላይ ሥራዋን የምታከብር ይሏታል። ይሄም በሥራዎቿ እንደሚታይ ምስክር ናቸው። ገጸባህሪን ቀድሞ በመረዳት የሚደርስባት የለም፤ ለትያትር ልምምድ ሲጀመር እሷ ገጸባህሪዋን ተረድታ በሚገርም ብቃት ለመተወን አፍታም አይፈጅባት። ታዲያ ይሄንን የተረዱ አብረዋት የሚተውኑ ከአዘጋጁም አልፈው አብረን እንለማመድ ብለው የሙጥኝ ይሏት ነበር።

የሷ ትወና ሙሉ ነውና አብሯት የሚተውነው ተዋናይ አብረዋት እንዲሞሉ ታደርጋለች። እሷ ስትተውን የተጻፈ ስክሪብት የምትሰራ ሳይሆን የዕለት ከዕለት ሕይወቷን



አርቲስት ባዩሽ አለማየሁ፤

**ከጀርመን መልስ እሷ የተወነችባቸው ሰማያዊ አይን፣ ነቃሽና ሰዓት እላፊን ያዘጋጀው ተፈራ ወርቁ በዚህ የዝግጅት ጊዜ ባዩሽ ምን ያህል አዘጋጅን የምታግዝ መሆኗን ማየቱን ጠቅሷል**

የምትኖር እንዲመስል አድርጋ ከራሷ ጋር ታዋህደዋለች። አብረዋት የሰሩ ተዋንያንም ሆኑ አዘጋጆች የራሷን ሥራ ቤቷ ጨርሳ እንደምትመጣ ይመሰክራሉ። ከራሷም ተርፋ ሌሌች ተዋናያን እንድታለማምዳቸው ስለሚመርጧት የአዘጋጅን ሥራ በማቅለል ትታወቃለች።

አብሯት አምስት ትያትር የሰራውና የሀገር ፍቅር ሥራ አስኪያጅ የነበረው አብዱልከሪም ጀማል "እሷ ነዳጅ ነበረች፣ ጉልበት ናት፤ እሷ መድረክ ላይ ካለች እራሷን ብቻ ሳይሆን አጠገቧ ያሉትንም አብረዋት የሚሰሩትንም ሰዎች እንደ ኢነርጂ የምታነሳና ከፍ የምታደርግ የመድረክ ፈርጥ ነበረች!" ሲል ረዥም ጊዜ ባገለገለችበት ሀገር ፍቅር ትያትር ቤት የእሷን ዕረፍት አስመልክቶ በተዘጋጀ የሽኝት መሰናድኦ ላይ ሀሳቡን ገልጿል።

ባዩሽ ተዋናይ፣ ደራሲ፣ አዘጋጅና ተራኪነትን አዳብሮ የቻራት ሁለገብ የጥበብ ሰው ነበረች። ከመድረክ ውጭ ሲያዩአት አጠር ደግሞም ቀጠንም ያለች ትመስላለች። የምትጫወተውን ገጸ ባህሪ ትልቅነት ለተረዳ ተመልካች እንዲያውም ያልተገባ ተዋናይ የተመረጠ ሁሉ ሊመስለው ይችላል። ግን ወደ መድረክ ስትወጣ ይሄ ሁሉ ይቀየራል። መድረኩን በግዝፈት ትሞላዋለች። "ገጽ ሁለት"፣ "ፎርፌ" እና "ረመጥ" የእርሷ ብዕር ውጤቶች ናቸው። በተለይ "ረመጥ" በ2008 ዓ.ም በተዘጋጀው የትያትር ፌስቲቫል ያሸለማትና በትወና ብቋቷም ሆነ በድርሰቷ በብዙዎች ዘንድ የምትታወስበት ሥራዋ ነው። ከጥበብ ሥራዋም በተጓዳኝ በነርሲንግ ትምህርት ተመርቃለች። በሀገር ፍቅር ትያትር ቤት የሚዘጋጁ ትያትሮችን የህክምና ጉዳዮችን በውስጣቸው ከነበረ ደራሲዎችም ሆነ አዘጋጆች ባዩሽን ማማከር ምርጫቸው ነበር።

በሀገር ፍቅር የምትወደው ትያትር ልምምድ ላይ ነበረች። በመሃል ትንሽ አመመኝ በማለቷ የሥራ ባልደረቦቿ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ሸገር ክሊኒክ ወሰዷት። ለመታየት በሄደችበት ክሊኒክ አልጋ ትያዝ ተባለ። በክሊኒክ የተጀመረው ህክምና ወደ የካቲት 12 ሆስፒታል ተሸጋገረ። ቤተሰቦቿም ሆነ የሞያ አጋሮቿ ሕመሟ ለሞት ያደርሳል ብለው አላሰቡምና በበርካታ አድናቂዎቿ ዘንድ የመታመሟ ዜና ሳይደርስ ታህሳስ 23 ቀን 2013 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞተ ተለየች። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በትያትር ጥበባት የመጀመሪያ ዲግሪዋን ለመውሰድ ለምርቃቷ ሸር ጉድ በምትልበት በ2013 ዓ.ም ሞት ቀደማት። የቀብር ስነ ስርዓቷም በቅድስት ስላሴ መንበረ ፀባኦት ካቴድራል ተፈፅሟል። አርቲስት ባዩሽ አለማየሁ በቲያትር ጥበብ ያላትን ልምድ ለማካፈልና ጥበቡን ከፍ ለማድረግ በምትችልበት እድሜዋ ብታልፍም የጥበብ ስራዎቿ ግን ዛሬም ህያው ናቸው።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ
ነፃ ሃሳብ
ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# የመፍትሄን ጠጠር - ሁሉም ይወርውር

ሰው መሆን

የኢትዮጵያ መንግስት ባለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት ውስጥ ለቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱን የሚያሳዩ እርምጃዎችን ሲወስድ አስተውለናል። ከእነዚህ ተግባራት ውስጥ ዘርፉን ከዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ውስጥ እንደ አንዱ በመቁጠር የፖሊሲ ማሻሻያ ማድረጉ ይጠቀሳል። ቀደም ባሉት ጊዜያት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር መጠሪያ ሁለት ዘርፎችን አጣምሮ የያዘውን አደረጃጀት በመነጣጠል ሁለቱም በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ደረጃ እንዲዋቀሩ ማድረጉ ሌላኛው የውሳኔው አካል ተደርጎ ይቆጠራል።

መንግስት በቱሪዝም ዘርፍ ከወሰዳቸው የፖሊሲ፣ የስትራቴጂ፣ የመዋቅራዊ አደረጃጀትና የሕግ ማሻሻያዎች በተጨማሪ በጥቂት ዓመታት ውስጥ አዳዲስ መዳረሻዎችን ማልማትና የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ማካሄድ ካከናወናቸው ውጤታማ ተግባራት መካከል ይጠቀሳሉ:: እነዚህ ስራዎች ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት በእርግጥም ተጨባጭና መሬት ላይ የወረደ መሆኑን ያመላክታሉ።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሀሳብ አመንጪነት በገበታ ለሸገርና ገበታ ለአገር ተገንብተው ወደ ስራ የገቡት እንዲሁም በገበታ ለትውልድ በሚል በግንባታ ላይ የሚገኙት ታላላቅ የመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶች የኢትዮጵያ ቱሪዝም መፃኢ ተስፋን ብሩህ እና ውጤታማ እንደሚያደርጉ የታመነባቸው ናቸው። ከአዳዲስ የመስህብ መዳረሻዎች ባሻገር ነባር የባህል፣ የታሪክ እና ሌሎች አርኪዮሎጂካልና የአርክቴክቸራል የኪነ ሕንፃ ቅርሶችን የመጠበቅ እና እድሳት የማድረግ ተነሳሽነትም እንዲሁ የመንግስትን ቁርጠኝነት የሚያመላክት በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው።

በመገናኛ ብዙሃንና ዘርፉን በሚመሩት የመንግስት ተቋማት አማካኝነት የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ ኢትዮጵያ የታሪክ፣ የባህል፣ የተፈጥሮ መልከዓ ምድር እና ሌሎችንም በርካታ ሀብቶች ከማልማትና ከመጠበቅ ያለፉ እርምጃዎች እየተወሰዱ ናቸው። ከእነዚህ መካከል መስህቦቹ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ትኩረት እንዲያገኙና ወደ አገሪቱ የሚገባው የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር ለማድረግ በመንግስት በኩል ሀብቶቹን የማስተዋወቅና በዩኔስኮ በዓለ ቅርስነት የማስመዘገብ ጥረቶች ይጠቀሳሉ። በዚህ ስራ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የባህል፣ የታሪክና የአርኪዮሎጂካል ሀብት የሆኑ ከአራት በላይ ቅርሶች ለዓለም ማስመዝገብ ተችሏል።

ከላይ በዝርዝር ያሰፈርኳቸው ውጤታማ ስራዎች በመጪዎቹ ጊዜያት የኢትዮጵያ የቱሪዝም ሀብቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት እንዲያገኙ ያስችላሉ፤ ይሁን እንጂ ለቱሪዝም እድገት፣ ለቅርሶች መጠበቅ፣ ለቱሪስት ፍሰት መጨመርና በጥቅሉ ለአገርና ለማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊና ሁለንተናዊ እድገት እነዚህ እርምጃዎችና ውጤቶች ብቻ በቂ አይሆኑም።

ለቱሪዝም ዘላቂ እድገት እነዚህ ውጤታማ ተግባራት በእጅጉ አስፈላጊ ቢሆኑም፣ ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ለማንሳት በፈለኩት በአንድ ቁልፍ ጉዳይ ምክንያት ግን የሚፈለገው ውጤትና በሚፈለገው ጊዜ ላይመጣ ይችላል። ይህ ለቱሪዝም እድገት በእጅጉ ወሳኝ የሆነው ጉዳይ እንደ እኔ ምልከታ ‹‹ሰላም›› ነው። ቱሪዝምና ሰላም አይነጣጠሉምና::

እንደሚታወቀው ቱሪዝም አንድ ሰው ለመዝናናት፣ ለህክምና እንዲሁም ለተለያዩ የግልና የቡድን ፍላጎቶችን ለማሳካት ሲል የሚያደርገውን የአጭር ጊዜ ጉዞ (ጉብኝት) መሰረት ያደረገ ነው። ይህ ማለት ሰዎች ከመኖሪያ ቤታቸው ወደ አንድ ራቅ ወዳለ ስፍራ ሲጓዙ በሚያወጡት ገንዘብ እና በጊዜ ላይ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም ሰዎች ለጉብኝትም ይሁን ለሌሎች መሰል ምክንያቶች ጉዞ ለማድረግ ሲያቅዱ ቅድሚያ ግምት ውስጥ የሚያስገቡት ደህንነታቸውንና የሚሄዱበትን አካባቢ ሰላማዊ ከባቢ ማረጋገጥ ነው።

በዚህ ወቅት እንበልና ለጉብኝት የመረጡት አካባቢ ሰላም እና መረጋገት ከሌለበት፤ በተቃራኒው ግጭትና ደህንነትን ስጋት ላይ የሚጥሉ ተግባራት ከበዙበት ጎብኚዎቹ የጉዞ እቅዳቸውን መሰረዛቸው ሳይታለም የተፈታ ነው። ይህ እርምጃቸው የሚሄዱበትን አገር አሊያም አካባቢን በቀጥታ የሚጎዳና ከጎብኚዎቹ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስቀር የዚያን አካባቢ ገፅታ በማጠልሸት ዘላቂ ጉዳት የሚያስከትል ይሆናል። በዚህ ምክንያት ነው ቱሪዝም ሰላም ከሌለ መሰረተ ልማት ቢገነባ፣ መዳረሻ ቢለማ በቂ እንደማይሆን አስረግጬ ለማስረዳት የሞከርኩት። ቱሪዝም ያለ ሰላም ‹‹አሳ ያለ ውሀ›› እንደማለትም ይሆናል።

የዘላቂ ቱሪዝም እድገት ያለ ሰላም እና መረጋጋት እውን እንደማይሆን መተማመን ላይ ከደረስን ወደሚቀጥለው ጉዳይ ማለፍ እንችላለን። አርሱም ኢትዮጵያ ውስጥ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚስተዋሉ አለመረጋጋቶችና ግጭቶች፣ ከቦታ ቦታ በሚደረግ እንቅስቃሴ ወቅት በታጠቁ ኃይሎች የሚደርሰው አፈና መንግስት በቱሪዝም ዘርፉ ላይ እያደረገ ያለውን ማሻሻያ፣ የልማት ስራና ከፍተኛ ትኩረት ይጎዳሉ::

በመግቢያዬ ላይ እንዳነሳሁት በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የቱሪዝም ዘርፍን እድገት የሚያረጋግጡ በርካታ ማሻሻያዎች ተወስደዋል። ይሁን እንጂ በአገሪቱ በተከሰቱ እና አሁንም ድረስ በሚታዩ አለመረጋጋትና ግጭቶች ምክንያት የተደረገውን ጥረት ወደ ኋላ የሚጎትቱ ተግባራት እየተመለከትን ነው። በማሻሻያዎቹ የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር እና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንዲሻሻል ይጠበቃል:: በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው አለመረጋጋት በቱሪስቶች ዘንድ ስጋትን የሚያጭር እና የጉዞ እቅዳቸውን ዳግም እንዲያጤኑ የሚያስገድድ ከባቢ እንዲፈጠር ያደርጋል::

በእርግጥ በእዚህ ሁሉ ስጋት ውስጥም ግን ወደ አገሪቱ የሚገባው የጎብኚ ቁጥር ከፍተኛ ነው:: የቱሪዝም ሚኒስቴር በተጠናቀቀው 2016 በጀት ዓመት ከአንድ ሚሊዮን በላይ የውጪ አገር ጎብኚዎችን ኢትዮጵያ ስለማስተናገዷ ካወጣው መረጃ መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው:: በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው አለመረጋጋት ከኢንዱስትሪው የሚጠበቀውን ያህል ኢኮኖሚ እንዳያመነጭ ትልቅ እንቅፋት ሆኗል። ይህ ሁኔታ ከሁሉም በላይ የአገር ውስጥም ሆነ የውጪ አገር ቱሪስቶች ለደህንነታቸው እንዲሰጉ በማድረግ በአገሪቱ ገፅታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳርፍ የሚችል ስጋትን ያጭራል።

**በመፍትሄው ላይ ስንመክር**

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በመንግስት የተወሰዱ በጎ የቱሪዝም ማሻሻያዎች በሰላም እጦት ምክንያት እንዳይሰናከሉ ሁሉም ባለድርሻዎች በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል። እንደሚታወቀው መንግስት ከቱሪዝም ዘርፍ ከግብር እና ከአንዳንድ የውስጥ የገቢ ምንጮች ውጪ በቀጥታ ገቢ አያገኝም፤ ማህበረሰቡ፣ የግሉ ዘርፍ እና ቱሪዝምን መሰረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ ሁሉ የዘርፉ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች ናቸው። ለእዚህም ሆቴሎች፣ የቱሪዝም ምርት አቅራቢዎች፣ አስጎብኚዎችና አስጎብኚ ደርጅቶችን በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

አንድ የቱሪዝም መስህብ ባለበት ስፍራ (እንደ ምሳሌ በትግራይ አክሱም፣ በአማራ ላሊበላ፣ በኦሮሚያ ባሌን መጥቀስ ይቻላል) የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ቱሪስቶች በስፍራው ሲገኙ የስራ እድል ይፈጠርላቸዋል፤ መሬት ላይ ያለው እውነታም ይህ ነው። ነገር ግን በዚያ አካባቢ ወይም ወደዚያ አካባቢ የሚወስድ መንገድ ባለበት አካባቢ ግጭት ሲነሳ ጎብኚዎች አይኖሩም፤ በዚህ የተነሳም ሆቴሎች፣ መዳረሻዎች የቱሪዝም ምርት የሚያቀርቡ ሱቆች፣ አስጎብኚ ደርጅቶች እና መሰል አካላት በቀጥታ ተጎጂ ይሆናሉ። ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው ይዳከማል፤ ስራ አጥ ይፈጠራል፤ ይበራከታል። ይህ በራሱ ይዞት የሚመጣው ሌላ ቀውስ አለ፤ ለማያቋርጥ የሰላም እጦትም ምክንያት ሊሆን ይችላል።

**አዳዲስ የመስህብ መዳረሻዎች ባሻገር ነባር የባህል፣ የታሪክ እና ሌሎች አርኪዮሎጂካልና የአርክቴክቸራል የኪነ ሕንፃ ቅርሶችን የመጠበቅ እና እድሳት የማድረግ ተነሳሽነትም እንዲሁ የመንግስትን ቁርጠኝነት የሚያመላክት በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው**

በመሆኑም መንግስት ሰላምና ደህንነትን የማስጠበቅ ቀዳሚ ድርሻና ኃላፊነት ቢኖርበትም፣ ህብረተሰቡም የራሱ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለበት ሊታወቅ ይገባል:: ከፍ ብለን እንደጠቀስነው በቱሪስቱ መምጣት የሚጠቀመው ህብረተሰብ ብዙ ነው:: ትራንስፖርት አቅራቢው፣ ሆቴሎች፣ አስጎብኚዎች፣ የቱሪስት ምርት አቅራቢዎች፣ ወዘተ በቱሪስቱ መምጣት በእጅጉ ይጠቀማሉ:: የቱሪዝም ስፍራው ኤኮ ቱሪዝም ሲሆን ደግሞ የህብረተሰቡ ተጠቃሚነት በእጅጉ ይሰፋል::

ይህ ሁሉ ህብረተሰብ የገቢ ምንጬ እንዳይቋረጥ፣ ስራ አጥነት እንዳይስፋፋ፣ የማንነቱ መገለጫ የሆኑ የባህል፣ የታሪክ፣ የቅርስ የአርኪዮሎጂና ሌሎች መስህብ ሀብቶቹ እንዳይወድሙ መጠበቅና መከላከል ይኖርበታል:: ለእዚህም በራሱም ከመንግስት ጋር በመተባበርም በአካባቢው ብቻ ሳይሆን ወደ አካባቢው የሚወስዱ መንገዶች፣ በጎረቤት አካባቢዎች ሁሉ ሰላም እንዲሰፍን አበክሮ መስራት ይጠበቅበታል።

የቱሪስት መስህቦችን የሚጎዳ፣ የቱሪስት እንቅስቃሴን የሚያስተጓጉል ጠላት ከሩቅ ብቻ አይመጣም:: በትናንሽ ጉዳዮች ያኮረፈ፣ የተቆጣም፣ የህብረተሰቡን መጠቀም የማይፈልጉ እንዲሁም ህብረተሰቡን በመጉዳት መንግስት የጎዱ የሚመስላቸው አካላት ተላላኪ የሚሆን የአካባቢው ሰው አይጠፋም:: እንዲህ አይነቶቹን ችግሮች ህብረተሰቡ ራሱ አስፈላጊ በሆነ ጊዜም ከመንግስት ጋር በመሆን ለመፍታት ትኩረት ሰጥቶ መስራት አለበት::

በኢትዮጵያ መቀመጫቸውን ያደረጉ ኢምባሲዎች፣ ቆንፅላ ፅህፈት ቤቶች እና አንዳንድ የዲፕሎማሲ ተቋማት አንዳንድ ኮሽታዎችን ሲሰሙ የውጪ አገር ዜጎች ለጉብኝት ወደ ተለያዩ የኢትዮጵያ መዳረሻዎች እንዳይንቀሳቀሱ፤ ከሄዱም ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በተደጋጋሚ ክልከላና ማስጠንቀቂያ እንደሚያወጡ ባለፉት ዓመታት ተመልክተናል::

በዚህ ክልከላ ሳቢያ አሁንም ድረስ ከዚህ ቀደም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጎብኚዎች በሚገኙባቸው በዓላት፣ ቅርሶች እና የተፈጥሮ መዳረሻዎች በአለመረጋጋቶች ምክንያት ጎብኚዎች አይገኙባቸውም፤ የዚህ ምክንያት የሰላምና መረጋጋት መጥፋት ነው። ይህ ደግሞ በዘላቂነት የአገር ውስጥም ይሁን የውጪ ቱሪስቶች እምነት እንዳይኖራቸው ተፅእኖ ያሳድራል። ሰላምና መረጋጋቱ ቢመለስ እንኳን ዳግም መልካም ስምና ገፅታን መልሶ ለመገንባት አዳጋች ሊሆን ይችላል።

እነዚህ ቁልፍ ችግሮች መንግስት በቱሪዝም ዘርፉ ላይ እየወሰደ ካለው የልማት፣ የጥበቃ፣ መስህብ የማስተዋወቅ ህግና ስርዓትን የማሻሻልና የመተግበር ስራ ባሻገር ተጨማሪ ኃላፊነት ወስዶ መስራት ያለበት ወሳኝ ተግባር እንዳለበት ያስገነዝባሉ። ሁኔታው መንግስት ሰላምና መረጋጋትን ከማረጋገጥ በተጨማሪ በዲፕሎማሲው መስክም እንዲሁ ብዙ መስራት እንዳለበት ያመለክታል:: ከሰላምና መረጋጋት እጦት ጋር ተያይዞ እንዲጠፋ የተደረገን ስም መመለስ ብዙ መስራትን ይፈልጋልና በዲፕሎሚሲው መስክም ብዙ ሊሰራ ይገባል::

ህዝቡ በተለይ ዳያስፖራው በእዚህ ጉዳይ ላይ በትኩረት መስራት ይኖርበታል:: መላ ሀገሪቱ በሰላም እጦት ውስጥ አይደለችም፤ የሰላምና መረጋጋት ችግር በስፋት የሚታይባቸው አካባቢዎች ይታወቃሉ:: ሰላምና መረጋጋት ወደ አለባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች ጉብኝት በማድረግ ይህንን ጉብኝታቸውን በተለያዩ መንገዶች ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጎብኚዎች እንዲታወቅ በማድረግ ሀገሪቱ ሰላም ያለባትና ለጎብኚዎች ምቹ መሆኗንም ማሳየት ያስፈልጋል::

መንግስት በአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ተፈጥሮ የሚፈለገው ውጤት እንዲታይ የሀብቱ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ ለሰላም ዘብ እንዲቆም ማስተባበር እና ተከታታይ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ማከናወንም ይጠበቅበታል። ማህበረሰቡ የሰላም እጦቱ ግንባር ቀደም ተጎጂ እንደሆነ በማስገንዘብ ሰላሙን እንዲጠብቅ ማድረግ ይገባል:: ሁሉም አካል የሰላም እጦት ይዞት የሚመጣውን የተራዘመ መዘዝ ለመከላከል በቅንጅት መስራት ይገባዋል።

# ዓለም አቀፍ

## ኢራን በሁሉም መስመሮች በረራዎችን አቋረጠች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እሥራኤል በትናትናው ዕለት በኢራን ላይ የወሰደችውን የአጸፋ ርምጃ ተከትሎ በቀጣይ መግለጫ እስኪሰጥ ድረስ ከኢራን የሚነሱም ሆነ በኢራን የሚያርፉ በረራዎች መቋረጣቸውን የኢራን ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን አስታወቀ።

በኢራን የአየር ክልል የሚደረግ በረራ ቆሟል። የሀገሪቱ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን ቃል አቀባይ ጃፋር የዝርሉ "በቀጣይ እስከናሳውቅ ድረስ ሁሉም በረራዎች ተቋርጠዋል" ብለዋል።

ኢራን መነሻ እና መዳረሻቸውን ወደ ሀገሪቱ ያደረጉ ሁሉንም በረራዎች እንዲቋረጡ መደረጋቸውን ገልጸዋል።




ቴህራን በረራዎች እንዲቋረጡ ያደረገችው በእሥራኤል ከተሰነዘረባት ጥቃት ከሰዓታት በኋላ መሆኑም ተመላክቷል።

የበረራ መረጃዎችን የሚያጋራው ፍላይት ራዳር የእሥራኤልን ጥቃት ተከትሎ የኢራን የአየር ክልል ከአውሮፕላኖች ነፃ መሆኑን የሚያሳይ ምስል አጋርቷል።

የኢራን አየር ኃይል እሥራኤል በቴህራን ኩዜስታን እና ኢማን ግዛቶች ሊፈጽመው የነበረውን ጥቃት ማክሸፍ መቻሉን ገልጿል።

በተወሰኑ አካባቢዎች መጠነኛ ጉዳት መድረሱን የጠቀሰው ታስሚን የዜና ወኪል በበኩሉ ቴህራን ለቴልአቪቭ ጥቃት አጸፋውን እንደምትመልስ መዛቷን ምንጮቹን ጠቅሶ አስነብቧል።

የእሥራኤል ጦር ቃል አቀባይ ዳኔል ሃጋሪ በሰጡት መግለጫ "እሥራኤል ግቧን አሳክታለች፤ እሥራኤልን የሚተነኩሱ ከባድ ዋጋ ይከፍላሉ" ብለዋል።

ቴህራን ሌላ ዙር ጥቃት በእሥራኤል ላይ ከፈጸመች ቴልአቪቭ ከበድ ያለ የአጸፋ እርምጃ እንደምትወስድ መናገራቸውንም ሬውተርስ ዘግቧል።

"መልዕክታችን ግልጽ ነው፤ እሥራኤል ላይ አደጋ የሚደቅንና ቀጣናውን ወደ ከፋ ውጥረት የሚከት አካል ከባድ ዋጋ ይከፍላል" ሲሉም ተደምጠዋል።

እሥራኤል የትናንትናውን ጥቃት የፈጸመችው በጥቅምት ወር መጀመሪያ ኢራን 200 በሚጠጉ ባለስቲክ ሚሳኤሎች ለፈጸመችባት አጸፋውን ለመመለስ ነው።

ቴህራን ግን ወታደራዊ ተቋማት ላይ ያነጣጠረው ጥቃት መጠነኛ ጉዳት ማድረሱን ከመግለጽ ውጭ እሥራኤል ስኬታማ ነበር ስላለችው የአጸፋ ጥቃት ጉዳት ዝርዝር መረጃ አልሰጠችም።

## ዘለንስኪ በብሪክስ ጉባኤ ተሳትፎ ምክንያት የተመድን ዋና ጸሐፊ የኪዬቭ ጉብኝት እቅድ ውድቅ አደረጉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ የተመድ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ በዚህ ሳምንት በሩሲያ በተካሄደው የብሪክስ ጉባኤ ላይ በመሳተፋቸው ምክንያት ኪዬቭን ለመጎብኘት የያዙትን እቅድ ውድቅ እንዳደረጉባቸው የዩክሬን ባለሥልጣን ተናግረዋል።

ኪዬቭ ባለፈው ሐሙስ በሩሲያዋ ካዛን ከተማ በተካሄደው ስብሰብ ላይ የጉተሬዝ መገኘት እና የጉባኤው አዘጋጅ ከሆኑት የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ፑቲን ጋር ሰላምታ መለዋወጣቸው አበሳጭቷታል።

የተመድ ምክትል ቃል አቀባይ ፋርሃን ሀቅ በብሪክስ ጉባኤ ሠላም እንዲመጣ ጥሪ ያቀረቡት ጉተሬዝ ባለፈው መስከረም ወር በኒውዮርክ ከዘለንስኪ ጋር በተገናኙበት ወቅት በዩክሬን ስለሚያደርጉት ጉብኝት ተወያይተው ነበር ብለዋል።

ሀቅ አክለውም እንደገለጹት ከእዚያ ጊዜ ጀምሮ ተመድ እና ዩክሬን ጉብኝቱ የሚያካሄድበትን ለሁለቱም ምቹ የሆነ ጊዜ የመምረጥ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። ነገርግን እስካሁን የተወሰነ ጊዜ የለም ብለዋል ቃል አቀባዩ።

አሁን ላይ ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ ጉተሬዝ በብሪክስ ጉባኤ በመሳተፋቸው ምክንያት ጉብኝቱን መሰረዛቸውን ሮይተርስ አንድ ስሙ እንዲጠቀስ ያልፈለገ የዩክሬን ባለሥልጣንን ጠቅሶ ዘግቧል።

የዩክሬን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለፈው ሰኞ እለት ጉተሬዝ የብሪክስን ጉባኤ እንዲሳተፉ የቀረበላቸውን ግብዣ መቀበላቸው የተመድን ዝና የሚጎዳ ነው ብሏል። ዘለንስኪ የጉተሬዝን መሳተፍ አውግዘዋል።

"ምንም እንኳን የተወሰኑ ባለሥልጣናት የካዛንን ስብሰባ ከተመድ ቻርተር ቢያስበልጡም፣ ዓለም የሀገራት መብት እና ዓለም አቀፍ ሕግ መከበር አለበት በሚለው መርሕ ላይ እንደጸና ነው" ብለዋል ዘለንስኪ።

ሩሲያ በዩክሬን ላይ በፈጸመችው "ልዩ ወታደራዊ ዘመቻ" በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሲገደሉ በሚሊዮኖች ደግሞ ተሰደዋል። ባለፈው ሐሙስ በሩሲያ የተካሄደው የብሪክስ ስብሰባ ዓላማው ምዕራባውያን ያልሆኑ ሀገራትን አቅም ለማሳየት ነው።



The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency



ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# አስገራሚ የእግር ኳስ ሕጎች

ቦጋለ አበበ



የእግር ኳስ ሕጎች ከመብዛታቸው የተነሳ አንድም ሳይቀር ሁሉንም ጠንቅቆ የሚያውቅ የስፖርቱ ባለሙያ የለም ማለት ባይቻልም፣ በእግር ኳስ ውስጥ ያሉ አሠልጣኞችና ፕሮፌሽናል ሰዎች ሁሉ ያውቋቸዋል ማለትም ድፍረት ይሆናል። ፊፋ በየጊዜው በርካታ ሕጎችን ያሻሽላል፡፡ የስፖርቱ ባለሙያዎችም እነዚህን የተሻሻሉ ሕጎች በየጊዜው እየተከታተሉ ራሳቸውን ከጊዜውና ከሁኔታዎች ጋር ማራመድ ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው፡፡

የዓለምን እግር ኳስ በበላይነት የሚመራው ፊፋ ካወጣቸውና በስፖርቱ ተግባራዊ ከሆኑ አስገራሚ ሕጎች መካከል አንዳንድ አሠልጣኞች እንዲሁም ፕሮፌሽናሎች ላያውቋቸው ይችላሉ ተብለው ከሚታሰቡ ሕጎች መካከል የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

# አንድ አሠልጣኝ ከፈለገ ለቡድኑ ሜዳ ገብቶ የመጫወት መብት አለው። ይህ ሕግ ብዙ ጊዜ ሲተገበር ስለማይታይ ብዙዎች ላያውቁት ይችላሉ። ይሁን እንጂ አሠልጣኝ የቡድኑ አንድ አካል እንደመሆኑ መጠን በተጫዋቾች ምትክ ወይም ተቀይሮ ሜዳ ገብቶ የመጫወት ሕጋዊ መብት አለው። ለዚህ ትክክለኛው ማሳያ ጂያንሉካ ቪያሊ ነው። ከዓመት በፊት በ58 ዓመቱ ሕይወቱ ያለፈው ጣሊያናዊው የቀድሞ የጁቬንቱስ ተጫዋች በ1990ዎቹ አጋማሽ በቼልሲ ቤት አሠልጣኝም ተጫዋችም ሆኖ ማገልገሉ ይታወሳል። ስለዚህ አንድ አሠልጣኝ አቅሙ እስካለው ድረስ ሜዳ ገብቶ ለቡድኑ ሲጫወት ቢታይ አያስደንቅም።

# በእግር ኳስ የረጅም ዓመታት ታሪክ አንድ ጨዋታ መምራት የጀመረ ዳኛ ጨዋታውን አጠናቆ ሲወጣ እንጂ እንደ ተጫዋቾች ተቀይሮ ሲወጣ ማየት የተለመደ አይደለም። ይሁን እንጂ በፊፋ ሕግ መሠረት አንድ ዳኛ የጀመረውን ጨዋታ ማጠናቀቅ የማይችልበት ችግር ከገጠመው በሌላ ዳኛ በተለይም በረዳት ዳኛ ተቀይሮ ሊወጣ እንደሚችል ተደንግጓል።

# ብዙ ጊዜ መስመር ዳኞች ከጨዋታ ውጭና የመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ዋናውን ዳኛ በማገዝ እንጂ ካርዶችን በመምዘዝ አይታወቁም። ይሁን እንጂ መስመር ዳኞች ካርድ ማሳየት የሚችሉበት አግባብ ግን አለ። ረዳት አሠልጣኞች ከዳኛ እይታ ውጪ የሆኑ ጥፋቶች (በተለይም ከሜዳ ውጪ ተጠባባቂ ወንበር አካባቢ ሊሆን ይችላል) ለሚፈጠሩ ችግሮች ረዳት ዳኞች ካርድ እንዲመዙ መጠየቅ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ረዳት ዳኞች በቀጥታ ካርድ አይመዙም፣ የዋናውን ዳኛ ይሁንታ ይጠብቃሉ። የዋናውን ዳኛ ይሁንታ ሲያገኙም በተመለከቱት ጥፋት ልክ የሚመጥነውን ካርድ መምዘዝ ይችላሉ። ረዳት ዳኞቹ ይህን ካርድ ቢመዙም ካርዱን ያሳየው ግን ዋናው ዳኛ ተደርጎ እንደሚቆጠር የፊፋ ሕግ 6 ላይ ተደንግጎ ይገኛል።

# አንድ ተጫዋች በቅጣት ምት፣ በማዕዘን ምት፣ በእጅ ውርወራ ወቅት ከጨዋታ ውጪ ቢሆን እንደ ጥፋት አይቆጠርበትም። በነዚህ አጋጣሚዎች ከጨዋታ ውጪ የሆነ ተጫዋች ኳስና መረብ ቢያገናኝ ይፀድቅለታል እንደማለት ነው። ይህን ሕግ ጠንቅቆ ባለማወቅ በአንዳንድ ሊጎች ላይ ተጫዋቾች የተቃራኒ ቡድን ተጫዋቾችን ከጨዋታ ውጪ ያደረጉ መስሏቸው ግብ ሲቆጠርባቸው የሚታይበት አጋጣሚ አለ።

# አንድ ተጫዋች ተቀይሮ እንደገባ ከቆመ ኳስ መሻማት እንጂ ጨዋታ ማስጀመር አይችልም። ይህ ማለት አንድ ተጫዋች ተቀይሮ ከመግባቱ በፊት ኳስ የእጅ ወይም የማዕዘን ምት ወጥቶ ከሆነ ልክ ተቀይሮ ሲገባ የወጣውን የእጅ ወይም የማዕዘን ምት (ኮርና) ኳስ ማሻማት ወይም ማስጀመር አይችልም።

# ግብ ጠባቂዎች እጅጌ ሙሉ ማሊያ መልበስ ይፈቀድላቸዋል። ነገር ግን በጨዋታ መሐል እጅጌ ሙሉው ማልያ አልተመቸኝም ብለው ወደላይ ከፍ ማድረግ ወይም መሰብሰብ አይችሉም። ይህን ያደረገ ግብ ጠባቂ ካርድ ይመዘዝበታል።